# የገጠር ኢትዮጵያ የልማት ሁኔታና ተስፋ

*አየነው እጅጉ፣ ከኢትዮጵያ ሣይንስ አካደሚ*

## 1. የኢትዮጵያ የግብርና ልማት ችግሮች

በለሙ አገሮች የእህል ሰብል ምርታማነት በአማካይ ከ 60 ኩንታል በሄክታር በላይ ቢሆንም፣ ዛሬም አርሶ-አደሩ የግብርና ዕውቀቱ የዛሬ 2000 ዓመት አካባቢ ከነበረው የቅርብ ምሥራቅ ጥንታዊ መሣሪያ **ስላልተላቀቀ**፣ ከምርጥ ዘርና ማዳበሪያ ጋር አማካይ የሰብል ምርታማነቱ ወደ 20 ኩንታል በሄክታር አካባቢ ነው፡፡ የ2011 የፌደራል መንግሥት የግብርና አፈጻጸም ዘገባ [2] እንዳሳየው፣ የ2011 የምርት ዘመን ምርታማነት መቀነስም ታይቶበታል፡፡ በሌላ በኩል፣ የወቅቱ የመንግሥት የግብርና ልማት መርህ ሰፋፊ መሬት ከከፍተኛ ድጋፍ ጋር ለኢንቬሰተር በሊዝ መስጠቱ፣ ከአርሶ-አደሩ የመሬት መጣበብና ከገጠር ሥራ-አጥ ወጣት መጨመርና በመሬት እጦት ምክንያት ወደ ከተማ መሰደድ ጋር አልተጣጣመም፡፡

የገጠሩን ሥራ-አጥ ወጣት መጠነኛ ሥልጠናና ድጋፍ ሰጥቶ፣ የበሬዎችን/ፈረሶችን ጉልበት የማይፈትን፣ ቢቻል የአሜሪካን የ19ኛ መቶ ዓመት ቀላል ማረሻ ዓይነት አዘጋጅቶ ማሠማራትና **ሰላምንና ኢኮኖሚውን መታደግ ሲቻል**፣ ለግብርና ኢንቬስተር ሰፋፊና ለም መሬት ማደሉ ብዙ አልጠቀመም፡፡ ከፍተኛ ትምህርት ከ60 ዓመት በፊት መሥርተን በዘመናዊ ግብርናም ትምህርት ዲግሪ እያደልን፣ ዛሬም የግብርና መሣሪያችንን 2000 ዓመታት ሙሉ አልቀየርንም። የበሬ ግንባር የምታህል መሬት ሰጥቶ፣ በልቶ ማደር ላቃተውና የመከራየትም አቅም ለሌለው አርሶ-አደር በሜካናይዜሽን ስም ምንም የማይፈይድለትን ኮምባይንም አምጥተንለታል እያልን፣ ይኸው በተከታታይ ዓመታት ራሳችንን እያታለልን ዛሬም በዘመነ ኮቪድ ስንዴ ከትርፍ አምራች አገሮች ለመግዛት እየሞከርን ነው። በቅርቡ ከግብፅም ገዝተናል።

በማረሻው ጥንታዊ መሆን ችግር ላይ፣ በመገናኛ ብዙሀን ተደጋግሞ እንደተነገረው፣ የምርጥ ዘርና የማዳበሪያ አቅርቦት ማጠርና ከአትራፊ ነጋዴዎች መግዛቱ፣ በልቶ ማደር በቸገረው ድሀው አርሶ-አደር ላይ የማዳበሪያ ዕዳ መክበድም በሰብል ምርታማነት ላይ ተፅዕኖ ሳያደርግ አልቀረም የሚል ግምት አለ ፡፡ ብዙ ሥራ-አጥ የገጠር ወጣቶችም ወደ አዲስ አበባ የሚመጡት ለቤተ-ሰብ ማዳበሪያ ዕዳ መክፈያ ገንዘብ ፍለጋ መሆኑን ይናገራሉ፡፡ ምርታማነት ባግባቡ አለማደግ፣ የምርትና የሕዝብ ዕድገት አለመመጣጠንና ፣ በ2011 ዓ.ም. ብቻ የ 11.1 ቢሊዮን ብር ስንዴ ተገዝቶ ወደ አገር በመግባት ላይ መሆን (ኢቲቪ 27/12/2011)፤ በኦሮሚያም ብቻ 10 ዞኖችና 90 ወረዳዎች የሴፍቲኔት ተጠቃሚዎች መሆን (ኢቲቪ 27/12/2011)፣ ምናልባት እየተባባስ ሊሄድ የሚችል የምግብ ዋስትናን ችግር ያመለክታሉ፡፡ ይህ የምግብ ዋስትና አለመኖር፣ በገጠሩ ዕድገት አዝጋሚነት ምክንያት፣ ለዋጋ ግሽበት መናርና ለኑሮ ውድነት፣ እንዲሁም ለወጪ ንግድ ከዓመት ወደ ዓመት መቀነስ፣ ለውጭ ምንዛሪ ከፍተኛ ዕጥረትና ለአግሮ-ኢንዱስትሪ መጋቢ ምርት ዕጥረት ዳርጎን፣ ከስንዴ ሌላ የምግብ ዘይት፣ ጥጥ፣ የቢራ ገብስ፣ ፍራፍሬና ሌላም በተገቢ ቅንጅት በወገናችን በዓመት ውስጥ በስፋት ሊመረት ሲችል ከውጭ አገር በተከታታይ መግዛት የተለመደ ሆኗል፡፡

በየፈርጁ የሚሠራ ብዙ ሥራ ያላት አገራችን፣ ሥራ-ፈጣሪ ትውልድ በማፍራት ፈንታ የትምህርት ሥርዓቱ የአገር ዕድገት ዓላማ ባለመያዙ፣ ትምህርት ለልማት መሣሪያ ከመሆን ይልቅ ለፖለቲካ በመዋሉ በትምህርት ጥራት ውድቀት፤ ምናልባትም በትምህርቱ ውጤት ተስፋ በመቁረጥ፣ ወጣቶች በብዛት ከት/ቤት የመቅረት (***በአማራ ክልል 20% ከት/ቤት ቀሩ ተባለ - የአማራ ቴሌቪዥን 2011***) ዝንባሌ አሳይተዋል። ባለፉት 4 ዓመታት ት/ሚኒስቴር 10.7 ቢሊዮን ብር ለክልሎች ድጎማ ሰጠሁ ቢልም (**ኢቲቪ 2011**)) በትምህርት ይዘት ላይ ለውጥ አለማምጣቱ አሳሳቢ ነው፡፡ ደካማ አሠራር በትምህርት ሥርዓቱ ላይ ብቻ ሳይሆን በግብርናውም ከብዙ ሺ ዓመታት ጥንታዊ ማምረቻ መሣሪያ ባለመላቀቃችን፣ የሕዝባችን ቁጥር እያደገ ሲመጣ ዘመናዊ አመራረት አብሮ እንዲያድግ ባለማድረጋችን ራሳችንን መመገብ ተቸግረናል፡፡

ገዢው ፓርቲ ደጋግሞ ዋናው የትግል አጋሬ ነው የሚለው የገጠሩ አካባቢ ልማትና ዕድገት ለዘመናት አዝጋሚ መሆኑና በተለይ የገጠር ድህነት መባባስ፣ (***በ2011 8.3 ሚሊዮን ሕዝብ የምግብ ዕርዳታ ተሰጠ - ኢቲቪ፣ 2011***)፣ የምርጥ ዘርና (**የዳውሮ ዞን ምርጥ ዘር ማጣትና በውድ ከነጋዴ ኢንዲገዛ መገደድ፤ በአማራ እንዲሁ - ኢቲቪ 2011**)፣ የማዳበርያም ዕጥረት (**ኢቲቪ 2011**) በተከታታይ ዓመታት መከሰትና ካልተጠበቀ ዝናብና ከብክነት ለመዳን ሰሜን ሸዋን ለመርዳት ያልተዘጋጀው የአማራ ክልል ግብርና ቢሮ ከደቡብና ከኦሮሚያ መሣሪያ ለመዋስ ማሰላሰሉ (***ኢቲቪ ኅዳር 12፣ 2012*** )፣ እንዲሁም የአርሶ-አደሩ ምርትና የገበያ ትሥሥር አለመኖር (**በኦሮሚያው ቦረና፣ ደቡብ ጎንደር፣ ደቡብ ወሎ፣ የኮንታ ልዩ ወረዳ ንብ አናቢዎች፤ የሰሜን ሸዋና የኦረሚያ ሽንኩርት አምራቾች - ኢቲቪ 2011** ) ዘመን-ዘለል ችግሮች ይመስላሉ፡፡ አጠቃላይ የግብርና ችግራችን በ2011 የምርት ዘመን ዘገባና በ2007-2011 ዓመታዊ የምርት [2,3] ዕድገት መዳከም ላይም ተንጸባርቋል፡፡

የግብርና ችግሮቻችን አንዱ አስከፊ ውጤት መሬት የሌላቸው ሥራ-አጥ የገጠር ወጣቶች አንድም ወደ ከተማና ወደ ውጭ አገር አደጋ የሞላበት የሞት ስደት ላይ ሲሆኑ፣ በአካባቢያቸው የቀሩት ደግሞ አንዳንዶች በመጠጥ ልማድ እንደተለከፉ፣ ከፊሎቹ በሌብነት እንደተሰማሩ፣ ከፊሎችም ከማህበረ-ሰቡ እንዳፈነገጡ የቅርብ ጥናቶች [11] አመልክተዋል፡፡ ዛሬ ላይ ለገጠር ሥራ-አጥ ወጣቶች የሚከፋፈል ተጨማሪ መሬት ስለሌለ፣ የሕዝብ ዕደገትም ቀጣይ ስለሚሆን፣ የትምህርት ሥርዓቱም ቀጣይ ስንኩልነት ተጨምሮበት፣ የገጠሩ ወጣት ሥራ-ፈት፣ ጠጪና ሌባ የመሆኑ ችግር እየጨመረ እንጂ እየቀነሰ ስለማይሄድ፣ ብዙ ሳይመሽብን የሥራ ዕድል በመፍጠር ለችግሩ አስቸኳይ መፍትሔ መፈለግ አለብን፡፡

ዛሬ ላይ ለሚታየው የዘመናት የተጠራቀመ የገጠር አገራችን ችግር መፍትሄው፣ በአንድ በኩል አርሶ-አደሩን የዕድገት ደረጃውን በሚመጥን ቴክኖሎጂ ወደ ዘመናዊ አምራችነት አፋጥኖ ማሸጋገርና ምርታማነትን አሳድጎ የገበያ ትስስሩን መገንባትና ዋጋ ማረጋጋት፣ በሌላ በኩል የገጠር የልማት ተቋማትን አግባብ ካለው ሥልጠናና ድጋፊ ጋር ማስፋፋትም

ለምግብ ዋስትናችንና ለኢኮኖሚውም የተፋጠነ ዕድገት ይበጃሉ፡፡ምናልባት የኢንዱስትሪ ፓርክን ያህል ወጪ ሳይጠይቁ፣ አገራችን ከ1996 እስከ 2005 የመደበችውን ዓይነት ባጀት ይዞ ወይም አሻሽላ መድብ ድጋፍ ሰጥታ፣ የግብርና መዛሪያ በደረጃችን አፋጥና መጥና አሻሽላ ***(ትራክተርና ኮምባይነር መሸመት ማለት አይሰለም።)***፣ የግብርና ግባቶችን አስተካክላ አቅርባ፣ የግብርና ሠራተኞችንም አሰልጥናና መጥና አሰማርታ፣ የግብርና ጥናትና ምርምርን ከአካባቢ ጥበቃ ጋር አጠናክራ፣ በከፍተኛ ደረጃ ተከታታይ የመንግሥት ዛይንዛዊ ክትትልና ቁጥጥር ቢደረግ በአጭር ጊዜ ውጤታማ መሆን ይቻላል፡፡

የግብርና ባጀት በ1996-2005 የ15 በመቶ ድርሻ የነበረው፣ በ2012 ወደ 3.75 በመቶ የወረደው፣ ምናልባት አገራዊው ባጀት በማደጉ የገንዘቡ መጠን ጨምሯል በሚል እሳቤ ከሆነ፣ አንድም የግብርናው የፌደራል ባጀት ድርሻ በጣም ስለወረደ፣ ሁለተኛም ከፍተኛ የዋጋ ግሽበት የ2012 ን የብር የመግዛት አቅም ወደ 1995 20 ሣንቲም አካባቢ ስላወረደው፣ ድህነትም በተከታታይ ዓመታት ሰለተባባሰ፤ ከሕዝብ ዕድገትና ከመዘናጋት ጋር የገጠመን አደገኛ የምግብ ዋስትና ማጣትና የውጭ ምንዛሪም ችግር የልማትና የደህንነት ማነቆ በመሆናቸው፣ የግብርናው ዓመታዊ ባጀት ድርሻ ወደ ቀድሞው 15 በመቶ አካባቢ ከፍ ሊል ይገባዋል፡፡ **ሕዝባችን ከመንግሥት የሚጠብቀው ከሰላም ማረጋገጥ ጋር በቂ ምግብና ለነፃነታችንና ለዘላቂ ዕድገት ዋስትና በመሆን ከቋሚ ጥገኝነት የሚያድነን ጥራት ያለው ዘመናዊ ትምህርት ነው፡፡**

ብዙ ለም መሬት፣ ሰፊ የውሀ ሃብትና ሠራተኛ አርሶ-አደር ይዘንም፣ የግብርና መዛሪያና አመራረት ባለፉት 2000 ዓመታት ስላላሻሻልን፣ <u>የገጠር ልማትና ጠቅላላ የአገርም ድህነት ቅነሳ በጥንታዊ አመራርና አሠራር አልተሳኩም</u>፡፡ **ሜጂ ጃፓን ለአያሌ ዘመናት የገዛትን ዘመነ መሣፍንት በአንጻራዊ ሰላም አስወግዳ የአገር ግንባታ ስትጀምር፣ አንድም ዩኒቬርሲቲ ሳይኖራት፤ አንድም ባንክ፣ ዘመናዊ ፋብሪካ፣ ነጋዴና የታክስ ሥርዓት ሳይኖራት፤ ዘመናዊ መንገድ፣ ስልክ፣ የፖስታ አገልግሎት፣መኪናና አውሮፕላን የሚባል ሳይኖራት፤ ከሞላ ጎደል በሀር፣ ሻይና ሩዝ ምርቶች ላይ ብቻ ተመርኩዛ፣ ሌት ተቀን በሠሩ አገር-ወዳድና ጀግና ልጆቿ ያላሰለሰ ትግል እአአ በ1868 ለውጥ ጀምራ በ14 ዓመት ውስጥ የጃፓንን ዘመናዊ የኢኮኖሚ መሠረት ግንባታ አሳከታለች፡፡**

## 2. የተለያዩ አገሮች የገጠር ልማት ጥረቶች

ከአንዳንድ የአፍሪቃ አገሮች በስተቀር፣ የሕልውናና የሉዓላዊነት ጉዳይ መሆኑን ተገንዝበው፣ የተለያዩ መንግሥታት ለግብርናው ዘርፍ ልዩ ድጋፍ በመስጠት፣ አርሶ-አደሮች የምግብ ዋስትናን ምን ጊዜም እንዲያረጋግጡ ያላሰለሰ ጥረት ያደርጋሉ፡፡ ከእነዚህ መካከል ቻይናን፣ አሜሪካን፣ የአውሮጳ ሕብረትንና ጥቂት የአፍሪቃ አገሮችን የገጠር ልማት ድጋፍና ጥረት በአጭር ባጭሩ ከዚህ በታች እናያለን፡፡

### 2.1. ቻይና

በምጣኔ ሃብት ባለሙያዎች [21] የሚነገሩትን የተለመዱ የልማት ቅድመ-ሁኔታዎችን በመጣስ፣

- ቻይና የገዢውን ፓርቲ ተግባር ከመንግሥቱ ሥራ በመለየት የዲሞክራሲያዊ ሥርዓት (የግል የፖለቲካ መብቶች፣ የዲሞክራሲያዊ ምርጫ ሥርዓትና የመንግሥትን ፈላጭ-ቆራጭነት የሚገድብ ሕገ-መንግሥት) ያልተገነባባት የሚመስል አገር ነው፡፡
- አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የቻይና መንግሥት በተሳከለት የንግድ ተቋም ላይም የፈለገውን እርምጃ የመወሰድ ሥልጣን አለው፡፡
- የንብረት ባለቤትነት መብት ማስከበሪያ ሕግም ሆነ የነጻ ገበያ ሥርዓት ያልተመሠረተበት የሚመስል አገር ነው፡፡

እንዲያም ሆኖ፣ እአአ በ1978 304.77 ቢሊዮን ኪሎ የእህል ምርት ያገኘችው ቻይና እአአ በ2015 621.44 ቢሊዮን ኪሎ እህል ምርት በማምረት በዓለም መሪ መሆኗ፣ የአርሶ-አደሩ የነፍሰ-ወከፍ ገቢ እአአ በ1978 **78 ዶላር** የነበረው እአአ በ2015 **1,834 ዶላር** መድረሱና በ38 ዓመት ***(ለዛሬው ድህነት ድርሻውን ያዋጣው ግራ-ዘመም የኢትዮጵያ አገዛዝ 45 ዓመት ሆነ፡፡)*** ውስጥ በያመቱ በአማካይ በ 8.7 በመቶ ማደጉ፣ እንዲሁም እአአ ከ2002 እስከ 2017 ባሉት 15 ዓመታት የቻይና ኢኮኖሚ በአማካይ ባመት በ9 በመቶ ማደጉ የድንቅ አመራር ውጤቶች ናቸው፡፡ የንብረት መብት ያልተከበረና የፖለቲካ ሥልጣን ያልተገደበ በሚመስልበት አገር፣ እውነታው ግን የቻይና ማዕከላዊ መንግሥት ለልማት ዕድገትና ለግል ሀብት መከበር ጠንካራ መሠረት በመጣሉ የግል ባለሀብት በቻይና ልማት ለመሳተፍ አልሰጋም፡፡ ለዚህም የረዳው፣ ያልተማከለ የፌደራል-መሰል አስተዳደር ሥርዓትና ገበያ-መር የግል ባለሀብትን ተሳትፎ የደገፈ ሥርዓት እአአ ከ1978 ጀምሮ በመፈጠራቸው፡-

- የቻይና አስተዳደር በማዕከላዊና በአውራጃ አስተዳደሮች መካከል የሥልጣን ክፍፍል ያለበት ሆኖ፣ በየሥልጣን ክልሉ ራሱን የቻለ አስተዳደር አለው፡፡
- የአውራጃ አስተዳደር የአውራጃውን ኢኮኖሚ ለመገንባት ከማዕከላዊ መንግሥት ፍጹም ነጻ ሲሆን፣ ማዕከላዊ መንግሥት ግን የጋራ ገበያውን የመቆጣጠርና የዜጎችን፣ የዕቃና ሸቀጣ-ሸቀጥ ዝወውር ነፃነት የማረጋገጥ ሥልጣን አለው፡፡
- በማዕከላዊ መንግሥትና በእያንዳንዱ አውራጃ አስተዳደር መካከል ያለው የተለያየ የገቢ ክፍፍል በሕግ ተገድቦ፣ ከባንክ የመበደር መብትም እንዲሁ የተገደበ ሆኖ፣ ይህ የሥልጣንና የኃላፊነት ክፍፍል በማዕከላዊ መንግሥትም ሆነ በአውራጃ አስተዳደር መለወጥ የማይችል ሆኖ የተደነገገ ነው፡፡

ይህ የመንግሥት መዋቅራዊ ለውጥ እአአ ከ1979 ተጀምሮ፣ በ1979 እና በ1991 መካከል የቻይና ኢኮኖሚ ባመት በአማካይ በ 8.6% አደገ፡፡ የእዚህ ዕድገት መሠረቱ በገጠር ትናንሽ ከተሞችና በገጠር መንደሮች እአአ ከ1958 ጀምሮ **<u>ለእርሻ መኪና</u>**

__ጥገና የተቋቋሙ የጥገና ማእከሎች ወደ አነስተኛ ኢንዱስትሪ ተቋማት መሸጋገር ነበር__ ፡፡ እነዚህ የገጠር ተቋማት ሙሉ በሙሉ በመንደርና ትናንሽ ከተማ ነዋሪዎች ባለቤትነት የተቋቋሙ፣ ከመንግሥት አመራር ነጻ የሆኑ፣ በገጠር ከተማ 3500 ቤተ-ሰብ ባለበት፣ በመንደር ደግሞ 200 ያህል ቤተ-ሰብ ባለበት፣ እአአ በ1992 በአማካይ እያንዳንዱ የትንሽ ከተማ ተቋም 66 ሠራተኞች የያዘ ፣ በጠቅላላ በአማካይ 8.2 የልማት ተቋማት (ENTERPRISES) ያሉት፣ በመንደርም እያንዳንዳቸው በአማካይ 23 ሠራተኞች ያሏቸው 1.4 የልማት ተቋማት (ENTERPRISES) የያዙ ነበሩ፡፡ እኒህ የገጠር ተቋማት፣ እአአ ከ1978 እስከ 1993 ባለው ጊዜ ከፍተኛ የኢንዱስትሪ ዕድገት በማምጣት በቻይና የኢኮኖሚ ዕድገት ሂደት መሪ ነበሩ፡፡

እነዚህ ***የከተማ-መንደር*** ተቋማት የማህበረ-ሰብ ተቋማት ስለሆኑ፣ የማህበረ-ሰቡ አስተዳደር (Community Government) በአስተዳደር ክልሉ ውስጥ ባሉ በመንግሥት ተቋማትና በግል ንግድ ድርጅቶችም ላይ ሙሉ ሥልጣን ነበረው፡፡ ነገር ግን በባንኮች ላይ ሥልጣን አልነበረውም፡፡ ስለሆነም፣ ከመንግሥት ነፃ መሆናቸው ቢረዳም፣ ገንዘብ ከባንክ ያለድርድር ማግኘት አለመቻላቸው ለማደግ ልዩ ከፍተኛ ጥረት ማድረግ እንደነበረባቸው ይታያል፡፡ ላይ እንደታየው፣ ሁለቱም ሁኔታዎች በማህበረ-ሰቡ አስተዳደር ተጨማሪ ጥረት እንዲደረግና የተሻለ ዕድገት እንዲገኝ ሳይገፋፉ አልቀሩም፡፡ እአአ በ1993 **የከተማ-መንደር ተቋማት ከአገሪቱ የኢንዱስትሪ ምርት የ36 በመቶ ባለቤት ነበሩ**፡፡ እነዚህ ተቋማት እአአ ከ1984 እስከ 1990 ምርታቸው በ65 በመቶ አድጓል፣ የሠራተኞችም ብዛት ተመጣጣኝ ዕድገት እንደነበረው መገመት ይቻላል፡፡ ሌላው የቻይና የሚደነቅ የኢኮኖሚ ዕድገት ዘርፍ ግብርናው ነበር፡፡

***ለግብርናው ዘርፍ የቻይና መንግሥት ድጋፍ***

የቻይና መንግሥትን ታምራዊ የገጠር ልማት ውጤት [4] ያመጣው እአአ ከ 1982 ጀምሮ እስከ ዛሬ በያመቱ __በቻይና ኮሚኒስት ፓርቲ ማዕከላዊ ኮሚቲ__ እየተዘጋጀ ***ተቀዳሚው ሰነድ ( No. 1 Document)*** ተብሎ በሚታወቀው የክትትልና ግምገማ ሰነድ እንደተዘገበው፣ በአገሪቱ ከፍተኛ የፓርቲ አካል ሳያሰልስ የተሰጠው ትኩረት ነው፡፡ የዚህ ሰነድ ይዘት በሶስት ይመደባል፡-

(ሀ) በጥናት ላይ የተመሠረተ የዓመቱ የገጠር ሕዝብ ችግር ትንታኔ፤
(ለ) በዓመቱ ውስጥ የተከሰቱት የገጠር ሕዝብ ችግሮች መፍቻ ውሳኔዎች
(ሐ) ለመንግሥት የተለያዩ ደረጃዎች የተሰጡ የችግር አፈታት ስልቶች መመሪያዎች

ናቸው፡፡ ለምሣሌ፣ እአአ በ2003 የአርሶ-አደር ዓመታዊ ገቢ መቀነስ በጥናት ስለተረጋገጠ፣ እአአ በ2004 የወጣው ***No. 1 Document*** ትኩረት ***" የአርሶ-አደሩን ገቢ ማሳደግ "*** የሚል ነበር፡፡ በፓርቲውም የተሰጠው መፍትሔ የግብርናውን መዋቅር ማስተካከል፣ ለአርሶ-አደሩ ገቢ ማሳደጊያ ተጨማሪ የሥራ ዕድል መፍጠር፣ የገጠርን መዋዕለ ንዋይ ፍሰት ማሳደግ፣ የገጠሩን ትራንስፎርሜሽን ማፋጠንና እርሻ-ተኮር የሣይንስና ቴክኖሎጂ ምርምር ማጠናከር ነበሩ፡፡ ስለሆነም፣ እአአ ከ2004 ጀምሮ፣ የቻይና እህል አምራች አርሶ-አደሮች ከመንግሥታቸው፡-

(ሀ) ቀጥታ የገንዘብ ድጎማ፤
(ለ) የምርጥ ዘር ስጦታ፤
(ሐ) የእርሻ መኪና ስጦታ

ማግኘት ጀመሩ፡፡ ይህ ድጎማ ቢያንስ ለ**600 ሚሊዮን አርሶ-አደሮች ይሰጣል**፡፡ ይህም የተደረገው፣ __**አንድም የምግብ ዋስትና ማረጋገጥ የቻይና ኮሚኒስት ፓርቲ ተቀዳሚ ተግባር ነው ብሎ በማመኑ**__፣ __**ሁለተኛም የቻይናን ሕዝብ 50 በመቶ አካባቢ የሆነው የአርሶ-አደሩ መራቆት ለሰላምና ለኢኮኖሚ ዕድገት እንደማይበጅ በመረዳቱ ነው**__፡፡ ይህ የቻይና ገዢ ፓርቲ ለአርሶ-አደር ገቢ መቆርቆር ለማንኛውም መንግሥት፣ __**በተለይም 80 በመቶ የገጠር ሕዝብ ላላት ኢትዮጵያ**__፣ የሚጠቅም አርዓያ ነው፡፡ ዛሬም ቻይና ለግብርናው ዘርፍ ሰፊ የገንዘብ ድጋፍ ትሰጣለች ፤ __**እአአ በ2015 ብቻ 248 ቢሊዮን ዶላር አደለች**__ __[15]__ ። __**ይህ ድጋፍ ከግብርና አምራቹ ጠቅላላ ገቢ 15 በመቶ ሲያህል፣ የጃፓንና ደቡብ ኮሪያ ወደ 50 በመቶ፣ የምዕራብ አውሮጳም ወደ 10 በመቶ ተጠግቷል፡፡**__

ይህ የቻይና ድጋፍ በተለይ የጥጥ፣ ቦቆሎና ስኳር ከፍተኛ መጠባበቂያ ክምችት ፈጥሯል፡፡ የቅርቡ የቻይና ተጨማሪ የድጋፍ መስመር ለአነስተኛ ገበሬዎች የሚሆን **ልዩ** __**የግብርና መኪና ለመሥራት ምርምር ማጠናከርና**__ የግብርናውን ዘርፍ ወደ ሮቦቲክስ ለማሸጋገርና የኩብት እበትም ወንዞችን እንዳይበክል የማጠናቀሪያ ሥርዓት መገንባት ሆኗል፡፡

### 2.2. አሜሪካ

በፈረስ እርሻ ላይ የተመሠረተውን ግብርናዋን ከ19ኛውም ክፍለ ዘመን ጀምሮ እጅግ ያሻሸለችው አሜሪካ፣ ለግብርናው ዘርፍ ይበልጥ ጠንካራ ድጋፍ መስጠት የወሰነችው የኢኮኖሚ ድቅቀት ስለገጠማት እአአ በ1933 Agricultural Adjustment Act (AAA) በተባለው ሕግ ነው ፡፡ ይህ የፌደራል መንግሥት ድጋፍ በእየአራት ወይም አምስት ዓመት በሚወጣ ሕግ (***FARM BILL***) ሲደገፍ፣ የመጨረሻው የእርሻ ሕግ (**AGRICULTURAL ACT OF 2014**) እአአ በ2018 አብቅቶ፣ ለቀጣዩም አራት ዓመታት ሰፊ የግብርና ምርት ክምችት ያላት አሜሪካ የ **867 ቢሊዮን ዶላር** ድጋፍ ለመስጠት ባላፈው ዓመት በፓርላማዋ ተደንግጓል፡፡ ድጋፉ የድሆችንና የግብርናን ዘርፍ ሰፊ ድጎማ ያጠቃለለ ነው፡፡

ድጋፉ እአአ በ2008 ላይ **640 ቢሊዮን ዶላር**፣ እአአ በ2013 **940 ቢሊዮን ዶላር**፣ የ2018 ደግሞ **867 ቢሊዮን ዶላር** መሆኑ፣ ከበርቴዋ አሜሪካ ለድሆች ዕርዳታና ለግብርናው ዘርፍ ያላትን ከፍተኛ ትኩረት አመልካች ነው፡፡ የተለየ ድጋፍ ከተሰጣቸው አያሌ አዝርዕት መካከል ከዓለም 3ኛ ትልቋ አምራች የሆነችበትና በዓለም መሪዋ የወጭ-ሻጪ (EXPORTER) የሆነችበት **ጥጥ** ነው፡፡ የአሜሪካ ድጋፍ ኦቾሎኒን፣ የወተት ምርቶችን፣ ስንዴን፣ በቆሎን፣ ሩዝንና አኩሪ

አተርንም ይጨምራል፡፡ በዓለም አሜሪካ በጥጥ፣ በቦቆሎ፣ በዳጉሳና አኩሪ አተር መሪ ወጭ-ሻጭ ***(EXPORTER)*** ስትሆን በሩዝም 3ኛ ነች፡፡ ግብርናና ተዛማጅ ተቋማት ከአገሪቱ ሠራተኛ 14 በመቶውን መያዛቸው፣ ከአገሪቱ ምርትም ***(GDP)*** 5 በመቶውን መሸፈኑ ያላሰለሰውና የጠንካራው የመንግሥት ድጋፉ ውጤት ናቸው፡፡ ከፍ ያለና ተከታታይ የግብርና ዕድገት እንዲኖር ለማረጋገጥ፣ እጅግ ጠንካራና ሀብታም ለሆነው የግብርናው ዘርፍ ከፍተኛ ድጋፍ በመስጠት መሪ የግብርና ምርት አምራችና ሻጭ አገር መሆን ችላለች፡፡

### 2.3. የአውሮጳ ሕብረት

የአወሮጳ ሕብረት የግብርና ድጎማ *(**COMMON AGRICULTURAL POLICY**)* የተጀመረው ከ2ኛው ዓለም ጦርነት ውድመትና በተከታታይ ከተከሰቱት ደካማ የምርት ዓመታት ለማገገም እንዲረዳ ነው፡፡ እንደ አሜሪካ ሁሉ፣ ***ተቀዳሚ ዓላማው ገበያ ለማረጋጋት፣ ትናንሽ አርሶ-አደሮችን ለመርዳትና የገጠር ልማትን ለማፋጠን ነው***፡፡

እአአ በ2019 የአውሮጳ ሕብረት የግብርና ድጋፍ **59 ቢሊዮን ዩሮ** ነው፡፡ ከዚህ ውስጥ የጀርመን፣ የፈረንሳይ፣ የእንግሊዝና፣ የጣሊያን፣ የሌሎችም ከበርቴ አገሮች ከበርቴ አርሶ-አደሮች ከባድ የገንዘብ ድጋፍ ያገኛሉ፡፡ የገንዘብ ድጋፉ ሁሉ-አቀፍ የግብርናን ሥራ ለመደገፍ ነው፡፡

### 2.4. አፍሪቃ

አስተካክላ ራስዋን መመገብ ባቃታት አህጉራችን፣ ለድሀ አርሶ-አደሮች የገንዘብ ድጋፍ የመስጠት አስፈላጊነት ገና በብዙዎቹ አገሮች ዘንድ ግንዛቤ ያገኘ አይመስልም፡፡ ከአፍሪቃ አገራት መካከል ግብጽ፣ ደቡብ አፍሪቃ፣ ናይጀሪያ፣ ማላዊና ሌሎችም ጥቂት አገሮች፣ ***ኢትዮጵያን ሳይጨምር*** ፣ የአርሶ-አደር ድጎማ እንደሚያደርጉ ይታወቃል፡፡ ከእነዚህ አገሮች መካከል ግብጽ ለጥጥ፣ ለሰኳርና ለስንዴ ምርት ልዩ ድጋፍ ትሰጣለችሀ፡፡

በቅርብ ዓመታት፣ የኢትዮጵያ ፌደራል መንግሥት ምርታማነትን ለማሳደግ፣ በትላልቅ እርሻዎችና በመንግሥት ተቋማት በኩል ትናንሽ አርሶ-አደሮችን ከዘመናዊ አሠራርና ቴክኖሎጂ ጋር ለማስተዋወቅና በገጠሯ አገራችን የሥራ ዕድል ለማስፋፋት በማቀድ፣ ለሰፋፊ እርሻዎች የታክስ ድጋፍና የመሬትና ሌላም ልገሳ በማድረግ፣ የመንግሥትንም አገልግሎት ለማቀላጠፍ ጥረት ቢያደርግም፣ በብዙሀኑ ድሀ አርሶ-አደር ድህነት ላይ ብዙ ለውጥ አላመጣም፡፡ ዛሬም ሰፊ ለም መሬት፣ ብዙ የውሃ ሀብትና ጠንካራ አርሶ-አደር እያለን፣ ***የምግብ ፍልጎታችንን በአንድ ወይም በሁለት ዓመት ውስጥ ማሟላት ሲቻል፣ ስንዴ፣ ስኳር፣ ጥጥ፣ የቢራ ገብስ፣ የምግብ ዘይትና ፍራፍሬ ከውጭ እየገዛን የውጭ ምንዛሪ ከምችታችንን እያራቆትንም*** **በወጭ ብድር ቋሚ ድጋፍ እንደነገሩ እየኖርን ነው**፡፡

እንዲያውም፣ ከወቅቱ የሰፋፊ እርሻ ባለውሎች መካከል አንዳንዶቹ የመንግሥትን አጠቃላይ የመሬት ሀብት ቁጥጥር ልልነት በመመርኮዝ፣ የተበደሩትን ብርም ባበደሯቸው የመንግሥት ተቋማት ፊት ለሆቴል ግንባታ አውለዋል ይባላል፣ ወይም ይዘውት እንደጠፉም ይነገራል፡፡ ይህን የባከነ ሰፋፊ መሬት፣ ሀብትና የዕድገት ዕድል መንግሥት ለሥራ-አጥ ወጣቶች አግባብ ካለው ሥልጠናና ድጋፍ ጋር ቢሰጥ ኖሮ፣ በራስ ከመተማመኑና ከዕድገቱ ዘላቂነት ሌላ፣ ምናልባት ዛሬ ላይ የውጭ ምንዛሪ ዕጥረትና የዋጋ ግሽበት ካሉበት ደረጃ አይደርሱም ነበር፡፡ ከበርቴ አሜሪካ፣ አውሮጳና ቻይና ለአርሶ-አደሩ ሰፊ ድጎማ የሚሰጡ ከውጭ ጥገኝነት ለመዳንና የአገርን ሉዓላዊነት ለማስከበር መሆኑ በጠቅላላው በአህጉራችን፣ ***በተለይም በኢትዮጵያ ዘንድ እስከ ዛሬም ግንዛቤ ያለ አይመስልም***፡፡ ባግባቡ ገጠሩን ለማልማት ሳይደክሙ፣ ከተሞችን በማብለጭለጭ ብቻ የገጠር ልማት፣ የምግብ ዋስትናና የውጭ ንግድ ዕድገት አይኖርም፡፡

የዛሬይቱ ኢትዮጵያ በያይነቱ ሊያበቅል የሚችል ድንግል መሬት፣ ሰፊ የውሀ ሀብትና ሰርቶ የማይደክም አርሶ-አደር ቢኖራትም፣ ***ማንኛውንም ሰብል አትረፍርፎ ለማምረት ከዓመት፣ ቢበዛ ከሁለት ዓመት፣ በላይ ባያስፈልግም***፣ በመንግሥት ትኩረት ማነስና የማያስተማምን የሰፋፊ እርሻ ልማት ባለቤት የሚሆን የውጭ ኢንቬስተር ፍለጋ በመጠመዳችን፣ ባለፉት ዓመታት ስንዴ፣ ቦቆሎ፣ ስኳር፣ የምግብ ዘይት፣ ጥጥና ፍራፍሬም ከውጭ በውድ ዋጋ በብዙ ቢሊዮን ብር መግዛቱን፣ አስከፊ የዋጋ ግሽበቱንና የውጭ ምንዛሪ ዕጥረቱን ተላምደን መኖር ከጀመርን ቆይቷል፡፡

ሀብታም አርሶ-አደሮችን ለሚጠቅሙ ከውጭ ለሚገዙ ለግብርና መሣሪያዎች የገቢ ታክስ መሰረዝና ለግባት ብድር መስጠቱ ቢኖሩም በልቶ ማደር የችገራቸውን ብዙሀኑን ድሀ አርሶ-አደሮች ባለመጥቀማቸው፣ በቂ ስንዴ፣ ቦቆሎ፣ ገብስ፣ ጥጥ፣ ፍራፍሬና ሌላም ማምረት አቅቶናል፡፡ የጎደለን አምራች ዜጋ፣ ለም መሬትና ውሀ ሳይሆን፣ ምናልባት ***ዋናው ቋሚ ችግራችን የግብርና ባጀት ዕጥረት፣ የግብርና መሣሪያ ኋላ-ቀርነትና ብዙሀኑ አርሶ-አደሮች በየጊዜው የሚገጥሟቸውን የግብርና ችግሮች ላይ ከቀበሌ እስከ ፌደራል ተቋማት ተቀናጅተው በፍጥነት መርዳት ባለመነሳሳታቸውና ባለመቻላቸው ነው***፡፡ እስከ ዛሬ ቀላል ሥራ ሆኖ የታየው ሰፊ ለም መሬት ከአነስተኛ ቁጥጥርና ሰፊ ብድር ጋር አቅም ያላቸው ለሚመስሉ ወገኖችና ለውጭ አገር ዜጎች መስጠት ነው፡፡ ይህ ውጤት-የለሽ የሰፊ መሬት ዕደላ መሬት አይከፋፈልም በተባለበት ወቅት በመሆኑ፣ መሬት የጠበባቸውንና የመሬት-የለሹን ብዙሀን ወጣት የሥራ-ፈትነት ችግርም ያላገናዘበ ነው፡፡

## 3. የቅርብ ዘመናት የኢትዮጵያ የግብርና ልማት ጥረቶች

የ2ኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ (2ኛው ዕትዕ፣ 2008-2012) ግቦች:-

1ኛ/ የምግብ ፍጆታን ማሟላትና የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ፣
2ኛ/ ለፋብሪካዎች ግባት በብቃት ማምረትና፣
3ኛ/ ለውጭ ገበያ በብቃት ማምረትና የውጭ ምንዛሪ ግኝት ማሳደግ ነበሩ፡፡

በዋና ዋና ሰብሎች (የአገዳ፣ ብርዕ፣ ጥራጥሬና የቅባት እህሎች) ምርቶች አኳያ፣ በ2007 የተገኘውን የ270.4 ሚሊዮን ኩንታል ምርት መነሻ በማድረግ ታቅዶ፣ በ2ኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የመጀመሪያ አራት ዓመታት የተገኙት ውጤቶች [2] የሚከተሉት ናቸው፡-

| የምርት ዓመት | የምርት መጠን በሚሊዮን ኩንታል | ከዕቅዱ የተሳካው በመቶኛ | ዓመታዊ የምርት ዕድገት በመቶ |
|---|---|---|---|
| 2007 | 270.4 | - | - |
| 2008 | 266.8 | 91 | -1.33 |
| 2009 | 290.4 | 91 | 8.84 |
| 2010 | 306.1 | 89 | 5.41 |
| 2011 | 315.6 | 78 | 3.10 |
| **በ2008-2011 አማካይ የዓመት ዕድገት** | - | - | **3.97** |

በቡና፣ በአትክልት፣ በፍራፍሬ፣ በአሣ ምርትና እንስሳት ተዋጽኦ ምርት፣ በተፈጥሮ ሀብት ልማትና በገጠር የሥራ ዕድል ፈጠራና እንዲሁም በግብርና ኮመርሺያላይዜሽንና ሜካናይዜሽን የተለያዩ ለስላሳ ውጤቶች ተገኝተዋል፡፡ በተለይ ከአገራችን 110 ሚሊዮን የሚገመት ሕዝብ 60 በመቶው አካባቢ ይመገበዋል የሚባለው ጤፍ የ2011 ምርት 50 ሚሊዮን ኩንታል ሲሆን፣ የአገሪቱ ፍላጎት ግን ከ 100 ሚሊዮን ኩንታል በላይ ነበር፡፡ በሙከራ በሄክታር ከ35 ኩንታል በላይ ተመርቶ ሳለ፣ በ2011 3.1 ሚሊዮን የጤፍ ማሣ ላይ 35 ኩንታል በሄክታር ቢመረት ኖሮ፣ ጠቅላላ የጤፍ ምርት ከ108 ሚሊዮን ኩንታል በላይ ስለሚሆን፣ የጤፍ ዋጋ በኩንታል 4000 ብር አካባቢ አይደርስም ነበር፤ በወጪ ንግድም በሚሊዮን ዶላር የሚቆጠር ገቢ ይገኝ ነበር። ከላይ በሠንጠረዡ እንደታየው ግን፣ የምርቱ የአራት ዓመት የዕቅድ አፈጻጸም በቂ አልነበሩም፡፡

በተለይ በ2011፣ ካለፉት ዓመታት በመማር፣ የተሻለ የእድገት ተስፋ የተሰነቀበት ቢሆንም፣ አፈጻጸሙ ደካማ ስለመሆኑ የአየር ንብረት ለውጥ፣ የሀብትና የማስፈጸም አቅም ውስንነት፣ የቴክኖሎጂ አጠቃቀም ውስንነትና የገጠሩ አካባቢ ሰላም መናጋት [2] በምክንያትነት ቀርበዋል፡፡ የዛሬ 2000 ዓመት ማረሻ የሚጠቀም፣ ከበጎች፣ ከዶሮዎች፣ ከላሞችና ጥጆች ጋር ጠባብ ጎጆውን የሚጋራ፣ በልቶ ለማደር የተቸገረ አርሶ-አደር ይዞ፣ ያለበቂ ድጎማና ድጋፍ የቴክኖሎጂ አጠቃቀቀም አፈጻጸሙ ባለፈው ዓመት ውስን ነበር ማለቱ፣ ዓመቱም ሳይጀመር የሚተነበይ ጉዳይ ነበር፡፡ የቴክኖሎጂ ጠቃቀም ሲባል የብዙሀኑን አርሶ-አደር የዕድገት ደረጃ የማይመጥነውን ትራክተርና ኮምባይነር ማቅረብ ከሆነ ምን ጊዜም አይሳካም።

የ2011 የምርት ዘመን ምርታማነት ቢበዛ የለማው ዓለም ምርታማነት ሩብ ያህል ሲሆን፣ የብርዕ ሰብሎች ምርታማነት ዕቅድ ሳይሳካ ቀርቷል፣ የጥራጥሬና የቅባት እህል የአንዳንድ ሰብሎች ምርታማነት ወርዷል፡፡ ያልተሳካው ወይም የቀነሰው መከሰት <u>**በመሣሪያ ኋላ-ቀርነት፣ በግባት ዕጥረት ወይም አጠቃቀም አለመስተካከል፣ በምርጥ ዘር ወይም በማዳበሪያ ዋጋ ውድነት፣ በተባይ መብዛት ወይም በሌላ ምክንያት**</u> መሆኑ በግብርናው ዘገባ አልተገለጠም፡፡ በመስኖ ልማት ድጋፍ፣ ከወይናደጋ ጋር ሲነጻጸር የቆላ ስንዴ ምርታማነት በ 33 በመቶ አድጓል ተብሏል፡፡ ይህን የስንዴ ግኝት <u>**በሜካናይዜሽን በመታገዝ በአፋር፣ ደቡብና ሶማሌ ክልሎች ብቻ**</u> ለማስፋፋት ታቅዷል፡፡ በለሙ አገሮች፣ ስንዴ እስከ 80 ኩንታል፣ አኩሪ አተር እስከ 100 ኩንታል፣ ቦቆሎ እስከ 120 ኩንታል በሄክታር ይመረታል፡፡ ሜካናይዜሽን ሲባል ግን ትራክተርና ኮምባይነር ከሆነ፣ አጣዳፊ የምግብ ችግር ለመቅረፍ ቢረዳ ነው እንጂ፣ ለኢትዮጵያ ድሀ አርሶ-አደር የሚመጥን አይደለም።

እንዲሁም፣ በሚመጣው ዓመት 20 የልዕቀት ማዕከላት በመገንባትና አስፈላጊ ማሰልጠኛ መሣሪያዎችን በማቅረብ፣ በጀርመን መንግሥት 50 ሚሊዮን ዩሮ እርዳታ ለአርሶ-አደሩ ጠንከር ያለ ሥልጠና ለመስጠት ዝግጅት እየተደረገ ነው ተብሏል፤ ነገር ግን ይህም ሆነ ሌላ መሰል በድሀው አርሶ-አደርና አርብቶ-አደር አቅምና አስቸኳይ ፍላጎት ላይ ካልተመሠረተ፣ ብዙ ለውጥ እንደማያመጣ መተንበይ ይቻላል፡፡ የድሀ አርሶ-አደር ሥልጠና ከተሚላና ተግባራዊ ድጋፍ ጋር ካልሆነ፣ የግብርናው ዕድገትና የገጠር ሕዝብ የድህነት ቅነሳ የትም አይደርሱም፡፡ የብዙሀኑ አርሶ-አደር ኑሮ ከእጅ ወደ አፍ በመሆኑ፣ መንግሥት የተሻሻለ ማረሻና የቴክኖሎጂውን ግባት ከተሟላ አጠቃቀም ጋር በራሱ ወጪ ካላቀረበላቸው በስተቀር፣ ሥልጠናው ብዙ ፋይዳ አይኖረውም፡፡ <u>**የእርዳታ ጋጋታ ብቻውን የገጠርን ሕዝብ ሕይወት አይለውጥም፡፡**</u>

የእውቀት መተግበሪያ መሣሪያና ግባት ከአርሶ-አደሩ አቅም በላይ ከሆነ፣ የመንግሥት ጥረት ጥቂት ትላልቅ አርሶ-አደሮችን ቢጠቅም ነው እንጂ፣ ከእርሻ በሬዎች/ፈረሶች ጋር ተጣጥሞ የተሻሻለ መሣሪያና የተለየ ድጎማ ካልተደረገላቸው ብዙሀኑን ትናንሽ አርሶ-አደሮች አይረዳም፡፡ በ19ኛው ክፍለ ዘመን ጃፓን በአጭር ጊዜ ከፍተኛ ዕድገት ያሳየችው <u>**የሰለጠነና አገር-ወዳድ የሰው ኃይል መንግሥት ካቀረበው መሣሪያና አስተማሪ ጋር በመቀናጀታቸው ነው**</u>፡፡ ባለፉት ዓመታት ምርት ለማሳደግ በግብርና ኤክስቴንሽን በኩል ብዙ ተደክሞ ምርት በመጠኑ ቢያድግም፣ በግብርና መሣሪያ ኋላ-ቀርነትና ግባት ዕጥረትና አጠቃቀም፣ በገበያ አለመረጋጋት፣ በመንገድ አለመኖርና በትራንስፖርት ዕጦት ምርት ወደ ገበያ ማምጣቱ ላይ ብዙ ችግር እንደነበረ በ2011 ጋዜጠኞች ብዙ ዘግበውበታል፡፡

በ2011 የግብርና ዓመት በ 188 ወረዳዎች **በስንዴ፣ በሰሊጥ፣ በጤፍ፣ በቦሎቄና በበቆሎ** የኩታ-ገጠም አመራረት መልካም ነበር በተባለ ውጤት ላይ በመመሥረት፣ በ2012 ዓ.ም. አሠራሩን ወደ 450 ወረዳዎች ለማሸጋገር ዕቅድ [1] እንዳለ ተዘግቧል ፡፡ ነገር ግን፣ ለእርሻ በሬ/ፈረስ የሚስማማ የተሻሻለ የእርሻ መሣሪያና የአመራረት መሻሻል፣ የግባት መሟላት፣ የምርት አሰባበሰብ፣ የተባይ ጥበቃ፣ የመጋዘንና የገበያ ትሥሥር፣ የዋጋ ማረጋጋትም ከሌለበት፣ ለዘመናት እንደታየው፣ ድሀው አርሶ-አደርና አገራችን ከድህነት አይወጡም፡፡

ሌላው በ2012 የተያዘው የኮመርሺያላይዜሽን ክላስተር ዕቅድ ድክመት፣ የአገሪቱን የግብርና ችግር በቁጥ-ቁጥ ለመፍታት **በአምስት ሰብሎች ላይ ማተኮሩ** ነው፡፡ ለኢንዱስትሪ ወሳኝ ግባት የሆኑትና የተለመዱት ጥጥና ገብስ የሉም፤ ብዙ የዕድገት ተስፋ የሚጣልበት የሩዝ ሰብል፣ ዋጋቸው በየጊዜው የሚያሻቅበው አትክልትና ፍራፍሬም የሉበትም፡፡ እንሰት ተረስቷል፡፡ የቡና ምርትን ጥቅም የማሳደጉና እያሽቆለቆለ መሄዱ ብዙ ያሳሰበ አይመስልም፡፡ የእንስሳት ተዋጽኦም ለአገር ውስጥና ለወጪ ንግድ ኢንዱስትሪ ወሳኝ ግብዓት መሆኑ በቂ ትኩረት አላገኘም፡፡ ከተለመዱ ጥሬ ሰብሎቻችንና የእንስሳት ውጤቶች ጋር **አዳዲስ አሰራሮች፣ አዋጭ ሰብሎችና ፍራፍሬዎች** እንዲመረቱ አልታቀደም፡፡ ቡና ማምረት ከጀመርን ዘመናት ቢያልፉም ክጥሬ ቡና አላለፍንም፡፡ ማንጎና አቮካዶ እንደ ዱር ፍሬ የሚታዩበት አካባቢም አለ፡፡ የለመድነውንም ባግባቡ ባለማምረታችንና የሕዝብ ብዛትም በማደጉ በተፈጠረ ዕጥረት፣ ከውጭ አገር በቢሊዮን ብር ስንዴና የምግብ ዘይት መግዛት ተለምዷል፡፡

ለግብርና የሚውል የሀብት ዕጥረት የለም፡፡ በ2012 ዓ.ም. ለከተማ ልማት 56.6 ቢሊዮን ብር ሲመደብ፣ ለግብርናና ለገጠር ልማት ከፌደራል ባጀት 3.75 በመቶ የሆነው 12.59 ቢሊዮን ብር ተመድቧል፡፡ የሕዝቡን 80 በመቶ ያህል ለያዘና የኢኮኖሚው ዋነኛ መሠረት ለሆነው የገጠር አካባቢ የበጀት ምደባው እጅግ አንሷል፡፡ ኢትዮጵያ እአአ ከ 2003/4 እስከ 2012/13 በያመቱ ከዓመት ባጀቷ 15 በመቶውን ለግብርና ትመድብ ነበር፡፡ የግብርና ምርቱ ተትረፈረፈ ተብሎ ይሁን ወይም በሌላ ምክንያት፣ በ2012 ዓ.ም. መንግሥት ለግብርና የመደበው ባጀት ድርሻ ወደ 3.75 በመቶ ወርዶ ከ 13 ቢሊዮን ብር በታች ነው፡፡ የአገር ሰላም፣ ክብርና ሉዓላዊነት ይቅሩብን ካላልን በስተቀር፣ **<u>ማንኛውም አገራዊ ልማት ከምግብ ዋስትናና ከግብ-ተኮርና የጠራ ትምሕርት በፊት ሊቀድም አይችልም፡፡ የሚበጀው፣ በከፍተኛ የመንግሥት ደረጃ ክትትልና ቁጥጥር የግብርና ምርትን አፋጥኖ ለማሳደግ፣ አንዱ ወሳኝ እርምጃ የግብርናንና የገጠርን ልማት ባጀት ማሳደግ ነው፡፡</u>**

ከአገር ምርት 35 በመቶውን ያህል ለሚያዋጣ የኢኮኖሚ ዘርፍ፣ ከ80 በመቶ በላይ የውጭ ምንዛሪ ለሚያስገኝ የኢኮኖሚ ዘርፍ፣ ከ80 በመቶ በላይ የአገሪቱን ሠራተኛ ለቀጠረ የኢኮኖሚ ዘርፍ፣ ከአገር ህልውናም አንጻር፣ በሩቁም ሆነ በቅርቡ ታሪካችን፣ ደሙን አፍስሶ፣ አጥንቱን ከስክሶ ነፃነታችንንና ሉዓለዊነታችንን ላስከበረና ዛሬም ሆነ ወደፊት ለሉዓላዊነታችንና ለአንድነታችን አሰተማማኝ ጋሻ ለሆነ ሕዝብ፣ የ 2012 የአዝመራ ዘመን የግብርናና ገጠር ልማት ቀጥተኛ ባጀት እጅግ አነስተኛ ነው፡፡ **<u>እንደ ቻይና መንግሥት አሠራርም</u>፣ ባለፉት ቅርብ ዓመታት ግብርናው በገዢው ፓርቲ ትኩረት ቢሰጠው ኖሮ**፣ ምናልባት የዛሬዋ ኢትዮጵያ የዋጋ ግሽበት፣ የውጭ ምንዛሪ ዕጥረት፣ የወጪ ንግድ የቁልቁል ሂደትና የወጣቶቻችን አስከፊ ስደትና የአገር ውርደት አይኖሩም ነበር፡፡ ብዙ የዓለም አገሮች ለኢንዱስትሪ ልማት የበቁት በግብርናው ዕድገት ላይ ተመርኩዘው ነው፡፡

ኢትዮጵያ ADLI እና PASDEP (እአአ 2002/3 – 2009/10)፣ GTP 1 & 2 (2007-2012) የተባሉ የልማት ዕቅዶች ነበሯት፡፡ በእነዚህ ዕቅዶች ግብርናንና ኢንዱስትሪን አጣጥሞ ለማሳደግ፣ ቀጥሎም ግብርናውን ገበያ-ተኮር ለማድረግና ከተሞችን ጨምሮ ባለሀብቱን ለማበረታታት፣ በመስኖም ለመጠቀም በተከታታይ የተቀየሱ የግብርና ልማት ዕቅዶች ነበሩ፡፡ ለስሳሳው የዕድገት ሙከራችንም ያልተሳካው፣ **<u>የዘመናት ችግሮችን ተሸክመን ዘመናትን በመግፋት ኋላ-ቀርነትንና ድህነትን በሁሉም የመንግሥት ደረጃ ቆርጠን ባለመጠየፋችን ነው</u>**፡፡ ዛሬ ላይ በፖለቲካው ሂደት ተስፋ ቢታይም፣ በኢኮኖሚው ግን ተመሳሳይ ተስፋ ለመሰነቅ፣ የኢኮኖሚውን ሂደት በሥራና አገር ወዳድነት፣ በጥናትና ምርምር ጥልቀት በዓለም ደረጃም በተመሰከረላቸው ባለሙያዎች እየመራች፣ **<u>በተፈተኑ የምጣኔ ሀብትና የግብርና ሣይንስ ሊቃውንት አማካሪ ጉባዔ</u>** እያስጠናች፣ ክልሎችንም ካላስተባበረች የተፋጠነ የገጠር ልማትና ሁለገብ የኢኮኖሚ ዕድገት ማምጣት አይቻልም።

## 4. የ 2012 የግብርና ልማት ዕቅድና የግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎት አፈጻጸም ሥልት (STRATEGY)

የዛሬይቱ ኢትዮጵያ፣ ለከተሜው ኑሮ ድጎማ በያመቱ ብዙ ቢሊዮን ብር የማውጣት አቅምና ልማድ ስላላት፣ ለኢኮኖሚውም ዋልታ የሆነውን የገጠር 80 ሚሊዮን የሚገመት ወገናችንን መኖሪያና የኢኮኖሚውን መሠረት ለመለወጥ፣ አደገኛ የገጠር ሥራ-አጥነትንና ስደትን፣ አስከፊ የዋጋ ግሽበትን፣ የውጭ ምንዛሪ እጥረትንና የወጪ ንግድን መቀነስ ለመቀልበስ፣ የአገሪቱን የምግብ ዋስትና ለማረጋገጥ (***Food Security***) ፣ የከተሜውንም ድጎማ ደረጃ በደረጃ ለመቀነስና ተቀናሹን ድጎማ ወደ ልማት ለማዞር፣ ለፖለቲካ ትርፍ ተብሎ ባለፉት 28 ዓመታት ለላሸቀና ዛሬም ላልተስተካከለ የትምህርት ሥርዓት ዘንድሮም 50.6 ቢሊዮን ብር የመደበች አገር፣ 80 በመቶ ለሆነው የሉዓላዊነቷ ጋሻ ለሆነው ሕዝቧ ልማት፣ **<u>ባለፉት 28 ዓመታት ገንቢ ውጤት ለከዳው የትምህርት ሥርዓት</u>** ከመደበችው <u>ቢያንስ ቢያንስ ከግማሽ በላይ</u> የመመደብ አቅም አላት፡፡

### 4.1. የ 2012 የግብርና ልማት ዕቅድ

**<u>የዓመት ባጀቱ ከ 13 ቢሊዮን ብር በታች ሆኖም</u>**፣ የ2012 የግብርና ዕቅድ [1] ምርታማነትን አሳድጎ፣ የምርጥ ዘርንና የማዳበሪያን አቅርቦት አሻሽሎ፣ የግብርና ሜካናይዜሽንን የልዕቀት ሥልጠና (**ምናልባት ለድሀው አርሶ-አደር በማይመጥነው ትራክተርና ኮምባይነር**) አጠናክሮ የተሻለ ዓመታዊ ምርት ለማግኘት ያለመ ነው፡፡ በ2011 ብዙ የምርትና ምርታማነት ግቦች ሳይሳኩ ቀርተዋል፡፡ ለዚህም የአፈጻጸም ችግር፣ የቴክኖሎጂ አጠቃቀም ውስንነት፣ ያልተረጋጋ አደረጃጀትና የአቅም ክፍተት በዋናነት እንደ ምክንያት ተጠቅሰዋል፡፡ **<u>2000 ዓመት ዕድሜ ያለው የግብርና መሣሪያ ኋላ-ቀርነት አልተነሳም</u>**። በአርሶ-አደሩና አርብቶ-አደሩ ላይ የከረመው የምርት ወደ ገበያ ማውጣቱ ከባድ ችግር በዚህም ዓመት የሚቀጥል ይመስላል፡፡ በ2011 ዓ ም በሁሉም ክልሎች አርሶ-አደሮችና አርብቶ-አደሮች ለደላላ ተዳረግን የሚለው እሮሮ በዛሬውም ዕቅድ ግልጽ መልስ አላገኘም፡፡ በአውሮጳ፣ አሜሪካና በእስያም የተለመደው ዓለም-አቀፍ ለግብርና ድጎማ የመስጠትም ልምድ ለኢትዮጵያ ድሀ አርሶ-አደርና አርብቶ-አደር ይጠቅማል ተብሎ የተገመተ አይመስልም፡፡ነገር ግን፣ ቢያንስ ቢያንስ፣ የምርጥ ዘር፣ የማዳበሪያና የግብርና መሣሪያ (ትራክተርና ኮምባይነር ሊሆን አይችልም።) ድጎማ አስፈላጊነትና የገበያ ችግር ትኩረት ሊያገኙ ይገባል፡፡

በእርግጥ **የግብርና ሚኒስቴር የ2012 ባጀት 12.59 ቢሊዮን ብር** [1] **ብቻ ነው** ተብሏል፡፡ 28 ዓመት ሙሉና ዛሬም የትምህርት ጥራትን በፖለቲካ ትርፍ ለለወጠና ዛሬም ላልተስተካከለ የትምህርት ሥርዓት 50.6 ቢሊዮን ብር መድቦ፣ በብዙ ቢሊዮን ብር ስንዴ፣ ስኳር፣ የምግብ ዘይት ማዳበሪያና ጥጥ በያመቱ ከውጭ የገዛ አገር፣ በምርት ዕጥረትና በምርት ስርጭት ሥርዓት ደካማነት ምክንያት አገር ያሰመረረ እስከፊ የዋጋ ግሽበት በናረበትና እንዲሁም የወጪ ንግድ ከዓመት ወደ ዓመት ቁልቁል በወረደበትና የውጭ ምንዛሪ ዕጥረት በከፋበት አገር፣ የግብርናውን እጅግ ጥንታዊ የእርሻ መሣሪያ ለማሻሻልና የግባት አቅርቦት ለማሟላትና ቢያንስ የ 2012ን 21 በመቶ የሰብል ዕድገት ግብ ለማሳካት፣ የምርትና የገበያ ትሥሥር ችግርን ለመቅረፍ፣ አርሶ-አደሩንና አርብቶ-አደሩንም ደጉሞ ለማበረታት የግብርና ሚኒስቴርን ባጀት በጣም ከፍ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡

ለገጠር የሥራ ዕድል መፍጠሪያ የቀረበው 50,000 ሄክታርና የ4 ቢሊዮን ብር የብድር አቅርቦት በተበዳሪዎች የቁጠባ አቅም ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ ***<u>ሥራ-አጥና መሬት-የለሽ ወጣቶች ቁጠባውን በታምር ያሳካሉ</u>*** የሚለውን በከፍተኛ ጥርጣሬ ብንቀበለውም፣ ከዛሬው በላይ በያመቱ እያደገ ለሚሄደው ሥራ-አጥ በተከታታይ ዓመታት ሰፊ ድንግል መሬት ይቀርባል የሚለው ምኞት ደግሞ ብዙ የማይመች ነው፡፡ ያለው መሬት ውስን ነው። የሚያዋጣው ጥንታዊውን የግብርና መሣሪያ አሻሽሎ፣ አምራቹን አነቃቅቶ፣ ምርታማነትን በከፍተኛ ደረጃ አሳድጎና ዋጋን አረጋግቶ መሬት ለጠበበው የምርት ዕድገት በማስገኘት፣ ለገጠር ሥራ-አጥና መሬት-የለሽ ወጣትም አነሥተኛ ኢንዱስትሪዎችን በገጠር በማስፋፋት ተሳታፊና ባለቤት በማድረግ የገጠር ድህነት ቀነሳ ማድረግ ነው፡፡ **<u>ምርታማነት የዛሬውን እጥፍ ቢሆን እንኳ፣ ብዙ ችግራችን በከፍተኛ ደረጃ ይቀንሳል</u>**፡ በእኛ አፈርና ውሀ የግብፅ ምርታማነት የእኛን እጥፍ ነው።

መንግሥት ለኢንዱስትሪ ፓርክ እንደሚሰጠው ዓይነት ድጋፍ፣ የአርሶ-አደሩንና የአርብቶ-አደሩን እስከፊ የዘመናት ድህነት ለመቀነስ የገጠር ልማትንም ባግባቡ ካደራጀ፣ በብቃት ከመራውና በከፍተኛ ደረጃ ክትትልና ቁጥጥር ካደረገ፣ ለገጠሩ ሥራ-አጥ ወጣት በያመቱ ሊያድግ የሚችል የሥራ ዕድል ስለሚፈጠር፣ **<u>የገጠር ኢንዱስትሪ ልማትም ለዘላቂ አገራዊ ዕድገት አጋዥና ለሰላምም ዋስትና ስለሚሆን</u>**፣ መንግሥት ይህን ወሳኝ ግዴታ ካልተወጣ፣ የገጠር ድህነት ቅነሳ ወይም የአገር ዕድገት፣ በልሂቃን **<u>ስብሰባና ልማዳዊ አመራር</u>** አይመጣም፡፡ ምስክራችን የገጠሩ አገራችን ድህነት ቋሚ መሆን ነው፡፡

የአርብቶ-አደሩና አርሶ-አደሩ ብዛት ግምት ቢያንስ 60 ሚሊዮን ነው ብንልና፣ ለ 1000 አርሶ-አደሮች/አርብቶ-አደሮች በየማሠልጠኛ ማዕከሉ ወይም በያምራች ማህበራት አንድ ወፍጮ፣ አንድ የማህበር ሱቅ፣ አንድ አነስተኛ የሰብልና የምርት መጋዘን **<u>ከፋብሪካና ወፍጮ መሣሪያ ጥገና ማዕከል</u>** ጋር ቢቋቋሙ፣ ሥራ ሲጀመር፣ ወደ 400,000 አካባቢ የገጠር ወጣቶች ሊቀጠሩ ይችላሉ፡፡ የመንግሥት መነሻ ወጪ በየማዕከሉ በወሮበላ ሳይበላ አንድ ሚሊዮን ብር ቢሆን፣ ጠቅላላው የመንግሥት መነሻ ወጪ ከ 10 ቢሊዮን ብር አይርቅም፡፡

በዚህ ላይ፣ ከታች እንደተጠቆመው፣ ሁሉም አካባቢ በመንገድና በመብራት አለመሟላት ምክንያት የገጠር ልማቱ በአንዴ ስለማይደራጅ፣ ከዘላቂ የገጠር ልማትና ድህነት ቅነሳ ጥቅሙና የገጠሩን የሴቶች የ2000 ዓመታት የጣዕር ሕይወት ከመለወጥ አኳያ ሲመዘን፣ የኢንዱስትሪ ምሥረታው ወጪ፣ በአንጻራዊነት፣ እጅግ በጣም አነስተኛ ነው ማለት ይቻላል፡፡ የሩቅ ምሥራቅ ስኬት ዋናው ምክንያት ኋላ-ቀርነትንና የኢኮኖሚ ጥገኝነትን ለማስወገድ **<u>በቁጬት የተነሳሳው ጠንካራ የመንግሥት</u>** ጥረት ነው፡፡ ተቋማቱ ተጠናክረው በእግራቸው እንዲቆሙ፣ መንግሥት ሀቀኛና ያላሰለሰ ጠንካራ ሥራ በየደረጃው በተከታታይ ዓመታት መሥራት አለበት፡፡

በማንኛውም ደረጃ ያሉ አመራሮች የአሠራር ሥርዓት ዘርግተው፣ ቢያንስ በያመቱ በመረጃ ላይ የተመሠረተ ጥብቅ ሣይንሳዊ ግምገማና እንደ አስፈላጊነቱ ማስተካከያ ሳያደርጉ፣ ከዓመት ወደ ዓመት ዕቅድ አልተሳካም እያሉ በያመቱ በየስብሰባ መዘገቡ የሚያመለክተው የዘጋቢውንና የሸዋሚውን የሥራ ቁርጠኛነት ማነስ ነው፡፡ **ቻይና [21] እና ጃፓን [5] ከ 15 ዓመት ባነሰ ጊዜ** የኢኮኖሚ መዋቅራቸውን ሲያዘምኑትና ወደ ሕዋም መንኮራኩር የላኩት ችግር ሳይገጥማቸው ቀርቶ አይደለም፡፡ **እኛ ግን ባለፉት 28 ዓመታት ለዘመናት ከነበርንበት ኋላ-ቀርነት እምብዛም ሳንነቃነቅ የ2000 ዘመናት ግብርና መሣሪያ እንኳ ሳንቀይር፣ ወርቃማ የልማት ዘመናትን በሚያስከፋ ሁኔታ አባክነን፣ ብዙ ለም መሬትና ሰፊ የውሀ ሀብት ቢኖረንም ዛሬም በምግብ እንኳን ራሳችንን አለመቻላችን ብዙ ያስተክዛል፡፡**

### 4.2. የግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎት አፈጻጸም ሥልት (STRATEGY)

በ2010 የተዘጋጀው የግብርና ኤክስቴንሽን የመስክ መዋቅር [16] 12,500 የአርሶ-አደር ማሰልጠኛ ማዕከሎች፣ 21 የልማት ወኪሎች - 10,000 አርሶ-አደር ለእያንዳንዱ የልማት ወኪል *(Development Agents)* - እና 25 የልማት ወኪል ማሠልጠኛ ማዕከሎች ያሉት፣ ዘመናዊ የግብርና ቴክኖሎጂን (ለብዙሀኑ ድሀ አርሶ-አደር ካቅሙ በላይ የሆኑት ትራክተርና ኮምባይነር ሊጨምር አይገባም።) በመጠቀምና ገበያ-መር ምርትን በማሳደግ የምግብን ዋስትና እና የአመጋገብ ሙሉነት ለማረጋገጥና ድህነትን ለመቀነስ ያለመ መዋቅር ነው፡፡ ስለሆነም፣ እያንዳንዱ የአርሶ-አደር ማሰልጠኛ ማዕከል በግርድፉ 1000 የሚያህሉ የአርሶ-አደር ቤተሰቦች የሚደግፍ ነው ብሎ መገመት ይቻላል፡፡

ይህ የ2010 የግብርና ኤክስቴንሽን የአሠራር ሥልት ከቀደመው ሥልት የሚለየው የሚመረቱት ሰብሎች ለገበያ ፍላጎት የተመቹ እንዲሆኑ የዕቅድ ትኩረት መስጠቱ ነው፡፡ ነገር ግን ገበያ-ተኮርነትን ተቀብሎ የምርትንና ገበያ ትሥሥሩን ከዋጋ መረጋጋት ጋር በመርህ ደረጃ የሚቀበል ቢመስልም፣ አርሶ-አደሩና አርብቶ-አደሩ ምርቱን እንዴት ለገበያ እንደሚያቀርቡና ስለ ዋጋ ማረጋገት ጉዳይም አስተማማኝ የግብይት አፈጻጸም ሥርዓት አያቀርብም፡፡ ለገበያ ችግሮች መፍትሔ ሳይሰጥ በነበረው የአሠራር ሥልት መቀጠል ለውጥ አያመጣም፡፡ ስለዚህ፣ ለዘመናት የቆየው የአርብቶ-አደርና የአርሶ-አደር የገበያና ተገቢ ዋጋ ዕጦት ችግር አሁንም በመገናኛ ብዙሀን ተደጋግሞ በ2011 እንደተሰማው፣ ቀጣይ መሆናቸው አልቀረም፡፡ ስለሆነም፣ በተለየ ጥረትና በኤክስቴንሽን አገልግሎት ጠንካራ ድጋፍ አርሶ-አደሩና አርብቶ-አደሩ የ 2000 ዘመናት ዕድሜ

ካለው ማረሻም ጋር ታግሎ ሻል ያለ ምርት ቢያገኝም፣ ምርቱን በገበያ ዋጋ ሸጦ መጠቀም ካልቻለና በያመቱ ለደላላ በአናሳ ዋጋ እንዲያስረክብ ከተገደደ፣ በቀጣዩ ዓመት የተሻለ የማምረት ጥረት ለማድረግ አይበረታታም፡፡ <u>**ከምርት አገልግሎቱ ጋር የተሻሻለ የግብርና መሣሪያ፣ የተቀናጀ የአዝመራ ጥበቃ፣ የምርት አሰባሰብ፣ ጥበቃ፣ ማከማቻና፣ ለፍትሐዊ ገበያ አገልግሎት የሚያበቃ የገበያ ትስስር ሥርዓትና አፈጻጸም**</u> ማደራጀት ያስፈልጋል፤ ማደራጀትም ይቻላል፡፡

የየዓመቱን ስኬት ለማወቅ፣ ካገሪቱ ሠራተኛ ሕዝብ 80 በመቶ ያህሉን የያዘውን <u>**የገጠሩን ሕዝብ ገቢ በያመቱ ከሌላው የኢኮኖሚ ዘርፍ ለይቶ መለካቱ አስፈላጊ ነው**</u>፡፡ መንግሥት በዘረጋው የግብርና ልማት ዘርፍ ያገኘውን ዕድገት በያመቱ ባግባቡ ሳይለካ፣ ሳያስተካክልና ድክመቱን ሳያርም ካመት ዓመት ከሞላ ጎደል በተለመደው መንገድ መቀጠሉ፣ ገጠሩን ለማልማትና ድህነትን ለመቀነስ አያስችልም፡፡ ብዙ አገሮች ከ20 ዓመት ባነሰ ጊዜ ለውጥ ካመጡ፣ ኢትዮጵያ ለምን በ 28 ዓመት እንዳቃታት በመንግሥትም መመርመር አለበት፡፡

ጅምሩ የቆየ ቢሆንም፣ ይህ የተሻሻለው የኤክስቴንሽን አገልገሎት አፈጻጸም ሥልት የግብርና ምርምርንና የኤክስቴንሽን አገልግሎትን ቅንጅት ለማጠናከር ከ2010 ዓ.ም. ጀምሮ ቅንጅቱ የሚሠራው በግብርና የእርሻ ልማት ሚኒስትር ደ-ኤታ ሰብሳቢነት <u>**በፌደራል የግብርና ልማት አካላት ግንኙነት አማካሪ ካውንስል**</u> ነው፡፡ የካውንስሉ አባላት ከግብርና ሚኒስቴር፣ ከፌደራልና የክልል ግብርና ምርምር ተቋማት፣ ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማትና ከሌሎችም ባለድርሻ አካላት የተውጣጡ ከ 80 ያላነሱ ናቸው፡፡ ይህ ካውንስል በዓመት ሁለት ጊዜ ተሰብሳቢ ሆኖ፣ አዲስ ቴክኖሎጂ በቀረበለት ጊዜ ምንጊዜም ለአርሶ-አደሩ ከመሰራጨቱ በፊት ጠቃሚነቱን በመስክ ሙከራ አረጋግጦ በግብርና ኤክስቴንሽን በኩል ለአርሶ-አደሩ እንደሚሰራጭ የአሠራር መመሪያው ያመለክታል፡፡ ይህ የፌደራል አሠራር የቴክኖሎጂ ግባት መጓተት እንዳያመጣ መጠንቀቅ ያስፈልጋል፡፡

ስለሆነም፣ አዲስ ግኝት ለዚህ ካውንስል በምርምር ተቋሙ መልካም ፈቃድ መቅረቡ ቀርቶ፣ **1ኛ**/ ሁሉም አባል የምርምር ተቋማት በየወሩ፣ በተወሰነ ፎርማት፣ የምርምር ሂደት ሪፖርት (**Progress report**) ለካውንስሉ ፀሐፊ (የግብርና ምርምር ዋና ዲሬክተር ናቸው፡፡) ቢልኩና፣ **2ኛ**/ ከፍተኛ የግብርና ባለሙያ የሆነው የካውንስሉ ፀሐፊ ለሙከራ የሚበቃ አዲስ ቴክኖሎጂ መቀበሉን ሲረዳ የካውንስሉ ስብሳቢ፣ ም/ሰብሳቢ፣ ፀሐፊ፣ አዲስ ቴክኖሎጂ ያቀረበው ተቋም ኃላፊና የቴክኖሎጂው ፈጣሪ ብቻ አዲሱ የቴክኖሎጂ ግኝት ወደ ሙከራ እንዲሸጋገር ቢያደርጉ ይበቃል፡፡ ከዚህም የሚሻለው ቴክኖሎጂውን ያቀረበው ተቋም በቀጥታ ሥራ ላይ አውሎ፣ ለካውንስሉ ዘገባ ቢልክና ባመቱ መጨረሻ ዝርዝር የትግበራ ዘገባ ቢያቀርብ ነው። በሙከራው መሠረት ቴክኖሎጂው ጠቃሚ ሆኖ ከተገኘ፣ የቀሩት የካውንስሉ አባላት ከዚያ ቴክኖሎጂ የተሻለ እንዲፈልጉ በዚሪ ማስታወቂያ ቢገለጽላቸው ወጪና የሥራ ጊዜ ብክነት ይቀንሳል፡፡

በተጨማሪ፣ ከተቋቋመ 10 ዓመት የሆነው የግብርና ትራንስፎርሜሽን ኤጀንሲ *(AGRICULTURAL TRANSFORMATION AGENCY)* ዛሬም ከወጪው ጋር የሚመጣጠን ለውጥ በአነስተኛው አርሶ-አደር ላይ ባለማምጣቱ፣ ይህን ድርጅት ዘግቶ፣ የግብርና መሣሪያና ግባቶችን አሻሽሎ፣ **የግብርና ምርምሩንና የግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎቱን አጠናክሮ በቅድሚያ ምርታማነትን በማሳደግ በአርሶ-አደሩ ላይ ለውጥ ማየት ይቻላል።** ባለፉት 10 ዓመታት በገጠሩ ድህነትና በአነስተኛው አርሶ-አደር ሕይወት ላይ ለውጥ ያላመጣን ተቋም በከፍተኛ ወጪ ተሸክሞ ከዓመት ዓመት መግፋት አይበጅም። የዚህ ተቋም ችግር፣ ምናልባት በውጭ አካላትና አመለካከት እየተዘወረ አገልግሎቱ ከአርሶ-አደሩና አርብቶ-አደሩ አቅምና ፍላጎት ጋር አለመጣጣምና <u>**በአንዴ ዘሎ የአውሮጳን ወይም የአሜሪካን ግብርና መሣሪያና ሥርዓት በልቶ ማደር ላቃተው አርሶ-አደርና አርብቶ-አደር ላስተዋውቅ ማለቱ**</u> ነው የሚል ግምት አለ ። የሚበጀው ለኢትዮጵያ የሚመጥን አገር-በቀል ቴክኖሎጂ በራስ ባለሙያ መፍጠር ነው። ግብርናን ገልብጠን ወይም አቋራጭ ወስደን ማሳደግ አንችልም።

## 5. የወቅቱ የሰው ኃይል ሥልጠናና የግብርና ልማት አካሄድ

ኋላ-ቀር የአገዛዝ ባህላችን ክስሕተት መማርን አጥብቆ ይሸሻል፡፡ እአአ በ 1858 ጃፓን ከምዕራባውያን ጋር እንድትነግድ ከተገደደች በኋላ፣ የጃፓን <u>**መሣፍንትና መኳንንት በሽንፈቱ በመቆጨት**</u>፣ ያገዛዝ ሥርዓት ለውጥ እአአ በ 1869 አድርገው የዘመናዊ ጃፓንን የኢንዱስትሪ መሠረት የጣሉት ከ 15 ዓመት ባነሰ ጊዜ [5] ነው፡፡ ኢትዮጵያ ግን ከመቅደላ ሽንፈት፣ ከአድዋ የወረራ አደጋ፣ ከማይጨው ሽንፈትና ከኢሕአዴግ *"መበስበስም"* በኋላ የአገዛዝ ለውጥ አደረገች እንጂ የዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ለውጥ አላየችም፡፡ <u>**ባለፉት 45 ዓመታትም ገዢዎቻችን ግራ-ገብ ፖለቲካ አንግበው፣ የግል ሥልጣንና የቡድን ጥቅም አስቀድመው፣ ዝም ብላችሁ ተገዙ አሉ እንጂ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ገንብተው ከችጋርና ጭቆና አላወጡንም**</u> ፡፡ የትምህርት ውድቀት 28 ዓመት ሙሉ ሲቀጥል አለማስቆማችን ሌላው ኋላ-ቀርነትን የመንከባከብ ምልክት ነው፡፡ <u>**ለማንኛውም የፖለቲካ፣ የማሕበራዊና የኢኮኖሚ ዕድገት ዋናው መሠረት ጥራት ያለው ትምህርት ብቻ ነው**</u>፡፡ ጥራት ያለው ትምህርት አለመኖር ሥራ-አጥ ያበራክታል፤ ኢንዱስትሪ፣ ንግድና አገልግሎት ያዳክማል፤ ድህነትን ያስፋፋል፤ የውጭ ጥገኝነት ያጠናክራል፤ በሉዓላዊነት ላይ ስጋት ያስከትላል፤ አገራዊ ዕድገት ያቀጭጫል፣ ሰላምም ያናጋል፤ የዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታንም ፈተና ውስጥ ይጥላል፡፡

ግብርናችንም ዛሬም 2000 ዓመት ዕድሜ ባለው በበሬ-ሞፈር-ቀንበርና በጥንታዊ ማረሻ መወሰኑ፣ አርብቶ አደሩም ግጦሽ ፍለጋ በየቀኑ ከመንደር መንደር መባዘኑ፣ በአፋር አሞሌ ጨው ዛሬም የሚቆረጠው በምሣር መሆኑ ያው ከለውጥ የመሸሽ ምልክቶች ናቸው፡፡ በቅርብ ዓመታት እስከ 2010 ዓ. ም. ያየናቸው ገዢዎቻችን ቢማሩም ባይማሩም፣ የኢትዮጵያን ሥር የሰደደ ኋላ-ቀርነትና የብዙሁኑን ወገናችንን ድህነት ለመቀነስ ካሉን ብቁ ምሁራን ጋር ለመሥራት ቁርጠኛነት አላሳዩም፡፡ እንዲያውም ብቁ መስሎ መታየትና ለብዙሀኑ መቆርቆር ከሥራ ለመባረር ምክንያት ነበረ፡፡ የኢትዮጵያ ችግር እንኳን የኢትዮጵያን ጥቂት ብቁ ዜጎች ይቅርና የዓለምን አያሌ ረቂቅ ሊቃውንትም የሚፈትን መሆኑ ግንዛቤ ያገኘ አይመስልም፡፡

ይህ ለባለሙያ ዕውቅና አለመስጠትና ማባረር፣ መማርን ትርጉም ያሳጣ ለዘመናት ኋላ-ቀርነታችንና ለተከታታይ የሁዓላዊነታችን መደፈር ሙከራ አንዱ ምክንያት ነው፡፡

ባለፉት ዘመናት የትምህርት **ጥራት በብዛት መተካቱ**፣ ዛሬም የወደቀውን የትምህርት ጥራት በተቻለ ፍጥነት በማስተካከል ፈንታ፣ በ2011 በቀረበው የትምሕርት ፍኖተ-ካርታ **900 ሁለተኛ ከፍተኛ ደረጃና** ሌሎችንም ት/ቤቶች ለመክፈትና **ጥራት-የለሽ ብዛት ዛሬም መመረጡ**፣ ከአንገብጋቢው የአገር ልማት ዓላማ ጋር ያልተጣጣመ ነው፡፡ በ2012 በጠቅላላ የመንግሥት የ1ኛና የ2ኛ ደረጃ፣ የሙያ ማሠልጠኛ ተቋማትና የ45 ዩንቬርሲቲዎች የትምህርት ባጀት 1.5 ቢሊዮን ዶላር ነበር። በአሜሪካ የአንድ አነስተኛና ደከምከም ያለ የመንግሥት ዩኒቬርሲቲ ያመት ባጀት ከ2.0 ቢሊዮን ዶላር በላይ ነው። በሠራተኛ ደመወዝና በተማሪ ቤትና ምግብ-ተኮር ወጪ ረገድ ብንለያይም፣ በላቦራቶሪ፣ በፍጆታ ቁሳቁስ፣ በመጻሕፍት፣ በምርምርና በአገልግሎት ድጋፍ የገበያ መሠረታችን አንድ ነው። ይህ የተራራቅ የባጀት ልዩነትና የትምሕርታችን ጥራት ውድቀት ምክንያት ባዋቂ ቡድን መመርመር አለበት።  **ከ45 ዩኒቬርሲቲ-መሰል ተቋማት** በላይ ይዞና የሕገ-መንግሥቱን አንቀጽ 52 በመተው የትምህርት አመራሩንም በፌዴራል መንግሥት ሥር ማስቀጠሉ፣ የዩኒቬርሲቲ ጥራት ቢረባም ባይረባም **በግድ ተማሪ መመደቡም** ትክክል አይደለም፡፡

ተማሪው ዩኒቬርሲቲ የመምረጥ መብት ያጣው፣ መንግሥት ያቋቋማቸውን አያሌ ተቋማት ደካማነት ለመሸፋፈንና ምደባ ባይደረግ ብዙዎች ደካማ ዩኒቬርሲቲዎች ባዶ እንደሚቀሩ ስለሚሰጋ ነው ብሎ መገመት ይቻላል፡፡ **ምደባው የተማሪንና የወላጆችን መብት የጣሰ፣ በከፈልም ቢሆን ተማሪ ከፍሎ የሚማር መሆኑን ያላገናዘበ፣ የአገርን ዘላቂ ጥቅምና ደህንነት የሰዋና ለደካማ ተቋማት ህልውና ጥብቅና የቆመ መርህ ነው**፡፡  ተጠያቂነት ባለው ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት የሌለና **የወላጆችንም ብስለትና ሁለ-ገብ አቅም ማነስ ተገን አድርጎ በወጣቶች፣ በወላጆችና በአገር የፈረደ መርህ ነው**፡፡የብዙ ባለሙያ ዕጥረት በየፈርጁ እያለብን፣ ምደባውን ተከትሎ መንግሥት በከፍተኛ ወጪ በዲግሪ ያስመረቀውን ወጣት በጉልበት ሥራ ማሰማራቱ የምደባውን ደካማነትም በግልጽ ያንፀባርቃል፡፡

ክልል እንሁን እያለ የሚወተውት አካባቢ የራሱን ተቋማት እንዲያስተዳድር ሕገ-መንግሥቱም ይፈቅዳል፡፡ ዩኒቬርሲቲዎችን በአላፊነት የተረከበ ክልል በወጣቱ ፈርዶ መህይም ከፈለፈለ፣ በሚመራው ሕዝብ ተጠያቂ ስለሚሆን፣ በሌላም በኩል በክልሎችም መካከል በጎ ውድድር ስለሚፈጠር፣ አገራዊ የትምህርት መርህ አውጥቶ በፌደራል መንግሥት ድጎማ ላይ ብቻ የአጠቃቀም ቁጥጥር ለማድረግ **አንድ የፌደራል ሚኒስቴር ብቻ አቋቁሞ**፣ የትምህርትን አስተዳደር አላፊነት ግን ለክልሎች መስጠት ኢትዮጵያን ይበልጥ ቢጠቅም እንጂ ከዛሬው የትምህርት ጥራት ውድቀት የባሰ አያመጣም፡፡ በውድድርና በተረጋገጠ ፍላጎት ላይ ተመሥርቶ የተሻለ የሰው ኃይል ሥልጠና በማድረግ፣ የገጠር ልማትም ሊፋጠን ይችላል፡፡ ዩኒቬርሲቲዎች የአካባቢ ባለቤትነት ቢኖራቸው፣ ለዩኒቬርሲቲዎች ሰላምም ይበልጥ ይጠቅማል፡፡ ባለፉት ዘመናት አንዱ የግብርና ልማት ማነቆም የሰው ኃይል ዕጥረት [2 ፣ 16] መሆኑ ተዘግቧል፡፡ ስኳር ኮርፖሬሽንም የራሱን ማሰልጠኛ ተቋም በቅርቡ ልከፍት ነው ያለው በትምህርት ተቋማቱ ሥልጠና ተስፋ በመቁረጥ ሊሆን ይችላል፡፡

በ 2011 ዓ.ም. መጀመሪያ የታደለው የ 14 ዓመት **ፍኖተ-ካርታ ማጠቃለያ** ***(Ethiopian Education Development Roadmap, 2017-30 –An Integrated Executive Summary)***፣ በትምህርት ሥርዓቱ ጥንካሬና ድክመቶች ዝርዝር ግምገማ ላይ፣ ከመንግሥት የወቅቱ የልማት መርሆዎች ጋር በማጣጣም  የንግዱን፣ የአገልግሎቱን፣ የአስተዳደሩን፣ የኢንዱስትሪውንና የገጠር ልማቱን የሰው ኃይል ፍላጎት በየመልኩ ከማሟላቱ ላይ፣ እንዲሁም ከዝርዝር ሥልታዊ አፈጻጸሙና የወጪ ዝርዝር ጥናትም ላይ ብዙ ይጎድለው ነበር፡፡ የትምህርት ሥርዓቱ የውድቀት ምንጭ የአገሪቱ ፖለቲካ፣ ኢኮኖሚና ማህበራዊ ቀውስ በመሆኑ ከአሜሪካም በመጡ ሆነ **በሌሎች ምርጥ የውጭ ምሁራን የሚጠገን አይደለም**፡፡ ይህ የ 28 ዓመታት ውድቀት ሊስተካከል የሚችለው፣ ሰፊ ልምድ ባላቸው፣ አገራዊ ጥናትና ምርምር ባደረጉ አገር-ወዳድ ዜጎቿና የሣይንስና ቴክኖሎጂ ኋላ-ቀርነቷን በሚጠየፍና የትምህርትን የልማትና ዘላቂ የዕድገት መሠረትነት በተቀበለ መንግሥት እንጂ፣ በአንጻራዊነት ለፖለቲካ፣ ለኢኮኖሚና ለማህበራዊ ህይወታችን ባይተዋር በሆኑ ጉበኚዎች አይደለም፡፡

እስከ ዛሬ ባለው አሠራር፣ የ45 የመንግሥት ዩኒቨርሲቲዎች ሥልጠና ተግባር-ተኮር አለመሆን፣ ከ 120 ዓመት በፊት ባቡር ብንገነባም፣ ያንን ባቡር በታትነን ወርውረን፣ ዛሬ ባቡር-መሰል ሥራ የሠሩልን **የዛሬ 120 ዓመት አካባቢ አብረውን ባቡር በአውሮፓውያን ዕርዳታ ያስገነቡት ሲሆኑ**፣ እኛ ግን ዛሬም ባግባቡ ተቆጣጥረንና እንዲጠቀምን አድርገን ማሠራትና የተሠራውንም ማምራት እንኳ መቸገራችን፣ የ2000 ዓመት ዕድሜ ባለው የግብርና መሣሪያ የእርሻ ልማት የማስፋፋቱ ዕቅድም አለመሳካቱ፣  የምግብ ዋስትና ማጣታችንና ለውጭ አገር የስንዴም ምርት ጥገኛ መሆናችን  **በሚኒስትሮች ም/ቤት በጥንቃቄ ሊመረመርና ፈጣን ማስተካከያ ሊደረግበት ይገባል**፡፡

በአብዛኛው በውጭ አገር ዜጎች የሚመራ፣ የአገርን የግብርና ምርት ትቶ የኢንዱስትሪ ግባት ከውጭ የሚገዛ የኢንዱስትሪ ፓርክ በብዙ ድካምና  ወጪ ሥራ ጀምሮ የውጭ ምንዛሪውን ችግር ካባባሰብን፣ ከነዚያውም በትርምስ መደናቀፉ የሚጠቁመው **አገር-በቀልና በአገር ልጆች የሚመራ የዕድገት ማጠናከሪያ** ሥልት አስፈላጊ መሆኑን ነው፡፡ የሚያዛልቀን የዕድገት ሥልት የአርሶ-አደርና አርብቶ-አደር ዜጎቻችንን ብቃትና ምርታማነት በተቀናጀ ድጋፍ **በፍጥነት ማሳደግና** በምርትና አሰባሰብና ጥበቃ፣ በጎተራ ሥራ፣ በገበያ ትሥሥርና ዋጋ ማረጋጋት ላይ አስተማማኝ ሥራ ሠርቶ ለምግብ ዋስትና ብቻ ሳይሆን ለምናልመው **ሁሉ-አቀፍ አግሮ-ኢንዱስትሪም** ግባት እንዲበቃ ማድረግ ነው፡፡ ከአርሶ-አደሩ አቅምና ሥምሪት ጋር ያልተቀናኛ ሥልጠናም ሆነ ተቋም የትም አያደርስም፡፡

በውጭ ዜጋም ሆነ በራሳችን ሰዎች የትላልቅ እርሻ ባለቤትነት ግብርናውን ማነቃቃትና ማዘመን ይቻላል የተባለው መንግሥታዊ መርህም እንዳልሠራ በብቃት ታይቷል፡፡ ትላልቅ እርሻ እናልማ የሚሉ የውጭ ዜጎችም ቢመጡ፣ ዋናው ግባቸው የኢትዮጵያን ዕድገት ለማጠናከር ሳይሆን፣ የመጡበትን ሕዝብ ወይም ፋብሪካ ጥቅም በእኛ ርካሽ ጉልበት፣ ለም

መሬትና ሰፊ የውሀ ሃብት ለማጠናከር ነው፡፡ አገራችንን የሚያዝልቀው፣ **<u>የአገር ልጆች መሪ ተዋናይ</u>** **<u>የሚሆኑበትን መንገድ አፋጥኖና ቅድሚያ ሰጥቶ</u>** ማመቻቸትና አስተማማኝና ዘላቂ **<u>የእድገት መሠረት መጣል ነው</u>**፡፡ ምሳሌያችን **<u>ጃፓን</u>** ነች።

ሌላው የግብርናችን ችግር፣ ከግብርና መሣሪያው ጥንታዊነት ሌላ፣ በሌላው ዓለም በሰፋት እንደሚደረገው፣ ለአርሶ-አደሮች የቴክኖሎጂ፣ የምርጥ ዘርና ማዳበሪያ መግዣ ድጎማ ባለመኖሩ፣ ለግብርና ግባትም መክፈል እያቃታቸው አርሶ-አደሮች ለእስር መዳረጋቸው፣ በብቁ ባለሙያ ድጋፍ ማጣት ብቻ ሳይሆን በግብዓት ውድነትም ምክንያት አጠቃቀማቸው የተሟላ ላይሆን ይችላል፡፡ ስለሆነም፣ አርሶ-አደሮች በገንዘብ እጦት ጭምር፣ ይበልጥ ምርታማ የሚያደርጋቸውን ምርጥ ዘርና ማዳበሪያ በብቃት ባለመጠቀማቸው ምርታማነታቸው ሊቀነስ ይችላል፡፡ ይህም በግብርና ሚኒስቴር የ2011 አፈጻጸም ዘገባ [2] ላይ የተዘገበው የምርታማነት ቅነሳ አንዱ ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡

**በሰንዴ፣ በሰሊጥ፣ በጤፍ፣ በቦሎቄና በቦቆሎ** የኩታ-ገጠም አመራረት ላይ ትኩረት በማድረግ፣ የግብርና ሚኒስቴር በ2012 ዓ.ም. አሠራሩን በ450 ወረዳዎች ብቻ ለማጠናከር ሲያቅድ፣ እንስት፣ ጥጥ፣ ገብስ፣ ሩዝ፣ አኩሪ አተር፣ ዘንጋዳ፣ ለውዝ፣ ኑግ፣ ጎመን ዘር፣ ተልባ፣ ጫቅማ፣ ሻይ፣ ቡና፣ ማር፣ ቅመማ-ቅመም፣ አትክልት፣ ፍራፍሬ፣ አሣ፣ የእንስሳት ተዋጽኦ ተመሳሳይ ትኩረት ያጡ ይመስላል፡፡ **<u>ከሰላም ማረጋገጥና ከአገር ሉዓላዊነት ማስከበር ጋር፣ የግብርናውን ልማት</u>** **<u>በሁሉም ወረዳዎች</u>** ማፋጠን ተቀዳሚው የመንግሥት ተግባር ነው፡፡ ባግባቡ ከተመደበ፣ ለገጠር ልማት የሚሆን የሀብት ዕጥረት የለም፡፡

ይህ የ2012 ዓ.ም. የግብርና ሚኒስቴር ዕቅድ የቆላ ስንዴ ሙከራ **በአፋር፣ በደቡብና በሶማሌ** ክልሎች የገደበውና 5 ሰብሎችንም በተወሰኑ ወረዳዎች ብቻ ለማስፋፋት የመረጠው፣ **<u>ምናልባት የግብርና ባጀት ትንሽ በመሆኑ ይሆናል</u>**፡፡ የግብርና ሚኒስቴር ትኩረትም በአምስቱ ሰብሎች ላይ ብቻ መወሰኑ፣ እንሰትንና ሌሎች ሰብሎችን፣ እንዲሁም የጨርቃጨርቅ ኢንዱስትሪን የዘነጋ ይመስላል፡፡ በወጪ ንግድ አኳያም፣ እንስሳትና የእንስሳት ተዋጽኦ፣ ማሽላ፣ አኩሪ አተር፣ አትክልትና ፍራፍሬ በማደግ ላይ ያለ የቅርብና የሩቅ ሰፊ ገበያ አላቸው፡፡ ባሉት ላይ **<u>ሌሎችም አዳዲስ ውጤቶች በየጊዜው ካልተጨመሩና ካልተጠናከሩን፣ የውጭ ምንዛሬ ፍላጎታችን ሁልጊዜ በውጭ ዕርዳታና በውጭ ከበርቴዎች በጎ ድጋፍና ስጦታ እንዲሟላ መጠበቅ ኋላ-ቀርነትንና ጥገኝነትን መንከባከብ ነው፡፡</u>**

ከግብርናውና ገበያ ማዘመን ጎን ለጎን፣ በግብርና ምርትና ተዛማጅ ልማት ላይ የተመሠረተ የገጠር ኢንዱስትሪ (**የዱቄት፣ ዳቦ፣ በርበሬ፣ ሽሮ፣ ቤት ግንባታ፣ የማሽን ጥገና፣ የመንደር ሱቅ፣ የሰብል መጋዘን፣ የወተትና የዶሮ ልማት፣ የተሻሻለ ሽመና፣ የብርና ጌጣጌጥ ሥራ፣ ንብ ማነብ፣ አዳዲስ የጓሮ አትክልትና ፍራፍሬ ልማት፣ ወዘተ**) በማስፋፋት፣ በማደግ ላይ ያለውን የገጠር ሥራ-አጥና መሬት-የለሽ ወጣት በኢንዱስትሪና በአገልግሎት ሥራ ላይ በማዋል፣ ወጣቱ ወደ አስከፊና አደገኛ ስደት፣ ወደ መጠጥና ሌብነት እያዘነበለ መሆኑን የቅርብ ጥናቶች [11] ያመለከቱትን አደጋ መቋቋም ይቻላል፡፡ በተያዘው የገጠር የሥራ-አጥ ፈጠራ ሂደት ከቀጠልንና የሥራ-አጡን ወጣት ችግር በተለያየ አዳዲስ የገጠር ልማት ጭምር ካላሸነፍን፣ ሰላም ሊጠፋ ይችላል፡፡

የኢንዱስትሪ ፓርኮችም ከአገሪቱ ምርቶች ጋር የጠበቀ ትሥሥር እንዲኖራቸው ተደርጎ ከተደራጁና **<u>ጥራት ያለው ሣይንሣዊ ቁጥጥርና ክትትል</u>** በመንግስት ከተደረገ፣ ገጠሩም አብሮ ያድጋል፡፡ የኢንዱስትሪ ፓርኮች ይበልጥ የሚጠቅሙን ደግሞ **<u>የአገር ልጆች መሪ ተዋናይ ሲሆኑ ብቻ ነው</u>**፡፡ እንደ ጃፓን የ19ኛው ክፍለ ዘመን ለውጥ፣ የአገር ልጆችን **<u>በብቃት መደገፍና ማነቃቃት</u>** [5]፣ እጅግ ፈጣን፣ ዘላቂና አስተማማኝ የኢኮኖሚ ዕድገት ያስገኛል፡፡ እንደ ከተማ መሬት አስተዳደር ልልና ልቅ አሠራር፣ መሬት መርጦ ኢንቬስተር ለተባለ ከማስረከብ ይልቅ ወጣቱን ደጋግፎ ማሳደጉ ይበልጥ ያዛልቃል፡፡ ባለፉት ዘመናት እንደታየው፣ ለውጭ የግብርና **<u>ኢንቬሰተር ቅድሚያ መስጠቱ ኪሳራን፣ ኋላ-ቀርነትንና ጥገኛነትን አራዘመ እንጂ የሚጨበጥ የገጠር ልማት አላስገኘም፡፡</u>**:

በአያሌ ክልሎችና ከተሞች (**<u>የቤኒሻንጉል ማንጎ፤</u> የፍኖተ-ሰላም ሎሚና ብርቱካን፤ የባህር ዳር ማንጎ፣ አቮካዶና ፓፓያ፤ <u>የሐረርና ድሬዳዋ ጊሸጣ</u>፣ ወሸመላ፣ ማንደሪን፣ ብርቱካን፣ ሎሚ፣ ማንጎ፣ ፓፓያ፣ ወይን፣ አቦከር፣ ካዝሚር፣ ወይን፣ ተምር፣ ወዘተ**) ውስጥና በአካባቢያቸው የጓሮ አትክልትና ፍራፍሬ ልማት በግብርና ኤክስቴንሽንና በየከተማው አስተዳደር በግልም ሆነ በሀብረት **<u>አ</u>**<u>ለመበረታታት</u> የኑሮ ውድነትን፣ ድህነትንና ሥራ-አጥነትን ቋሚ አድርጓል፡፡ የአትክልት (***ቃሪያ፣ ሽንኩርት፣ ካሮት፣ ቀይ ሥር፣ ጎመን፣ ሰላጣ፣ ቆስጣ፣ ዱባ፣ ወዘተ***)፣ የፍራፍሬ (***ኮክ፣ ማንጎ፣ አፕል፣ ወሸመላ፣ ብርቱካን፣ ተምር፣ ሙዝ፣ ሎሚ፣ ወይን፣ ጥሩን፣ አቮካዶ፣ ካዝሚር፣ አቦከር፣ ፓፓያ፣ ማንደሪን፣ ትርንጎ፣ ወዘተ.***) የዶሮ ርቢና ወተት ልማት ማበረታታት **<u>በከተማ ሹሞቻችን አልተለመደም</u>**፡፡ በየጓሮው ዶሮ እርባታ፣ አትክልትና ፍራፍሬ የማብቀል ዕድል አለ፡፡ እንደ አዲስ አበባ ያለ ባለብዙ ሀብትና ባለሰፊ ገበያ አስተዳደርም፣ ብዙ ሥራ-አጥ በአትክልት፣ ፍራፍሬና ዶሮ ርቢ ሥራም ጭምር ሊያሠማራ ሲችል፣ አለዚያም ሌላ ሥራ በጥራት ማሠራት ሲቻል፣ አደባባይ ደጋግሞ አፍርሶ መገንባቱና የእግር መሄጃ ነገ እንዲፈርስ አድርጎ መሥራቱ ለሥራ-አጥነትና ድህነት ቅነሳ አይረዱም፡፡

## 6. የገጠር ኢንዱስትሪ ልማት ምክረ-ሃሳብ

የገጠር የእርሻ መሬት ተጣብቦ ቢያንስ 4,000,000 የገጠር ቤተሰቦች፣ 35 በመቶው [11]፣ ግማሽ ሄክታርና ከዚያ በታች ስላላቸውና ብዙ የገጠር ወጣትም መሬት-የለሽ ስለሆነ፣ ብዙ ወገኖቻችን ከረሃብ አፋፍ ላይ በመሆናቸው፣ መሬት ያነሳቸው አርሶ-አደሮችም፣ እንደ ንጉሡ ዘመን ከምርታቸው ከሩብ እስከ ሲሶ በመክፈል ፈንታ ግማሹን [11] ለባለመሬት ማስረከባቸውም፣ አማራጭ የሥራ ዕድል በአስቸኳይ እንዲፈጠር ማስፈለጉን ይጠቁማሉ፡፡ እያንዳንዳቸው 1000 ያህል አርሶ-አደር ቤተሰቦች ባሉባቸው፣ **<u>በማምረቻ ማህበራትና ለግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎት በተደራጁት 12,500 የአርሶ-አደር ማሰልጠኛ ማዕከሎች</u>**፣ የግብርና ግብዓቶችን ማከፋፈል፣ ለኢትዮጵያ ድሀ አርሶ-አደርና አርብቶ-አደር የሚመጥን የግብርና ሜካናይዜሽንን ማስፋፋት፣ የመሣሪያ ጥገና ማዕከል ማስተዳደር፣ የባህል ሥራዎችን (**ሽመና፣ የብረታ ብረትና**

***ጌጣጌጥ፣የስፌት ሥራዎች፣ ወዘተ***) ማነቃቃት፣ የንግድ ተቋማትንና ጥቃቅን ፋብሪካዎችን እንደ አካባቢው ምቹነት፣ አቅምና የምርት ዓይነት በቅደም ተከተል መከፈትና ፈጣን የገጠር ኢንዱስትሪ ዕድገት በመጀመር መሬት ለጠበባቸው አርሶ-አደር ቤተሰቦችና ለመሬት-የለሽ የገጠር ወጣቶች **<u>በብቁ አመራር</u>** ብቁ ድጋፍና ሥልጠና ሰጥቶ የገጠር ዕድገት ማፋጠን ይቻላል፡፡ የገጠር ኢንዱስትሪ መከፈትና ማበረታታት፣ በለሙ አገሮችም የተለመደ የዕድገት መሸጋገሪያ አሠራር ነበር፡፡

የገጠሩ ብዙሀን እናቶች ዘላለም የወፍጮ መጅ ሲወቅሩና ቀኑን ሙሉ ሲፈጩና ሲወቅጡ፣ ውሀ ከየሸጡ በጀርባቸው ሲሸከሙ፣ ወደ ገበያ ቅርጫት በጀርባቸው ተሸክመው ምርት ሸጠውና ገዝተው ተሸክመው ዛሬም ሲመላለሱ፣ ከአውድማ ምርት በጀርባቸውና በትክሻ ተሸክመው እስከ ዛሬ ሲያበሉን፣ አይዟችሁ ብሎ ሸክማቸውን ያቃለለላቸው አስተዳደር አላገኙም፡፡ ለገጠር ሕዝብ አገልጋይና አጋር ነኝ የሚል አስተዳደር ይህን አስከፊ የዘመናት ሸክም ማቅለል ግዴታው ነው፡፡ ዛሬም ከ 2000 ዓመት በፊት የነበሩት እናቶች የኖሩትን አስከፊ ሕይወት ይገፋሉ፡፡ ስለሆነም፣ እስከ ዛሬም አርሶ-አደሩ፣ ጾታ ሳይለይ፣ የኢኮኖሚ ዋልታ፣ የሉዓላዊነታችን ዋስትናና የከተሜውም አለኝታ መሆኑ በቂ ትኩረት አላገኘም፡፡

ገጠሩን ለማልማት፣ ለምሣሌ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት እንደ አካባቢው ምቹነት(***መብራት፣ መንገድ፣ ስልክ፣ ውሀ መኖር***)፣ አቅምና የምርት ዓይነት እየተለዩ ደረጃ በደረጃ በአገር-ወዳድ፣ ብቁ አመራርና ያላሰለሰ ከፍተኛ የመንግሥት ክትትልና ቁጥጥር ስኬታማ ሆነው እንዲያድጉ ሆነው ሊቋቋሙ ይችላሉ፡፡

- *የግብርና ግባቶች፣ የምርትና የሸቀጣ-ሸቀጥ መደብር*
- *የዱቄት፣ በርበሬና ሽሮ ወፍጮ፤*
- *የምግብ ዘይት ፋብሪካ*
- *የጥጥ መፈልቀቂያ ፋብሪካ፣*
- *የፍራፍሬ ማዘጋጃ ፋብሪካ*
- *የአናጢና የብረታ ብረት ሥራ (የሰውና የዕቃ ጋሪ ማጓጓዣና ሌላም)፣ የፋብሪካና የግብርና ዕቃዎች ጥገና ማዕከል*
- *የባህል ዕደ-ጥበባት ድጋፍ ማዕከል*
- *የደን ጥበቃና የውሀ ውጤታማ አጠቃቀምና ልማት*

እነዚህ ተቋማት ለዓይነት ተዘረዘሩ እንጂ፣ ለሁሉም አካባቢ ይስማማሉ ወይም እነዚህ ይበቃሉ ለማለት አይደለም፡፡ ለምሣሌ፣ ጥጥ መፈልቀቂያ ፋብሪካ በደጋ የልማት ማዕከል ቦታ የለውም፡፡ ጥጥ ሳይኖርም የጨርቃጨርቅ ፋብሪካ ማቋቋምም ለጥጥ አብቃይ አገሮች ሲሳይ መሆን ነው፡፡ መንግሥት የገጠርን ልማት ሲያጠናክር የግሉም ባለሀብት ተከታትሎ ይመጣል፡፡ መጀመሪያ ግን፣ መንግሥት ከልማዳዊ አመራርና አስተዳደር መላቀቅ አለበት፡፡

### 6.1. የገጠር ኢንዱስትሪ ልማት የመዋዕለ-ንዋይ ፍላጎትና ምንጭ

ከላይ የተገለጡት የገጠር ልማት ማዕከሎች፣ **<u>የቀበሌ ልማት ድርጅቶች</u>** ቢባሉ፣ **<u>ከማምረቻ ማህበራት ጋር</u>** የአርሶ-አደሩ ማሰልጠኛ ማዕከሎች ስለሆኑ፣ ቁጥራቸው ቢበዛ **12,500** [16] ነው፡፡ በገጠሪቱ ኢትዮጵያ በግብርና ብቻ የተሰማራው ሕዝብ ብዛት 60 ሚሊዮን ያህል ቢገመትና እያንዳንዱ የገጠር ቤተሰብ በአማካይ 5 አባላት ቢኖሩት፣ የገጠሩ አርሶ-አደር ቤተሰብ ብዛት 12 ሚሊዮን አካባቢ ይሆናል፡፡ ይህ 12 ሚሊዮን አርሶ-አደር ቤተሰብ ለ 12,500 የኤክስቴንሽን ሥልጠና ማዕከላት ሲካፈል፣ በእያንዳንዱ ማዕከል ሥር 1000 ያህል አርሶ-አደር ይኖራል ማለት ነው፡፡ ስለሆነም፣ የልማት <u>ምቹነት፣ አቅምና የምርት ሁኔታ እየታየ በሥራ ላይ የሚውል መነሻ ባጀት</u>፣ በእያንዳንዱ ማዕከል ላይ አንድ ሚሊዮን ብር ለተቋማት ግንባታ(ለዱቄት፣ በርበሬ፣ ሽሮ ፍጮ፣ ለሸቀጣ-ሸቀጥ ሱቅ፣ ለማዳበሪያ፣ ምርጥ ዘርና ለምርት ማከማቻ መጋዘን፣ ለግብርናና ለወፍጮ መሣሪያ ጥገና ማዕከል፣ ወዘተ) በሌባ ሳይበላ ቢውል፣ ጠቅላላ የገጠር ኢንዱስትሪ ዕድገት መሠረት መጣያው የመንግሥት ወጪ 12.5 ቢሊዮን ብር አካባቢ ይሆናል፡፡

ይህ ገንዘብ በአንዴ የሚወጣ ሳይሆን፣ የቀበሌ ልማት ድርጅት የተቋቋመበት ወረዳ መሠረተ ልማት ***(መብራት፣ መንገድ፣ ውሀ፣ ስልክ፣ ወዘተ)*** መሟላት፣ የሕዝቡ ፍላጎትና ዝግጁነት፣ የምርት ዓይነትና መጠን እየታየ ደረጃ በደረጃ የሚወጣ ነው፡፡ ልማቱን **<u>በቁጭትና ከአገርና ሕዝብ ፍቅር</u>** ጋር ወገንና አገር ለማሳደግ የሚጥሩ ሹማምንት ሲመሩት፣ **<u>ጠንቃቃ የዞንና የክልል ሥራ በክልል ም/ቤትና በሚኒስትሮች ም/ቤት ቁጥጥር ከተሠራ</u>**፣ በጥቂት ጊዜ ውስጥ የእያንዳንዱ የአካባቢ የቀበሌ ልማት ድርጅት ሠራተኛ ቁጥር ወደ 50 ሊያድግ ስለሚችልና በጎረቤት ድርጅቶች መካከል ውድድር በመፍጠር እያንዳንዳቸው ወደ ትልቅ ኩባንያነት ሊያድጉ ስለሚችሉ፣ ከጥቂት ጊዜ በኋላ በሚሊዮን የሚቆጠር ሠራተኛ ቀጣሪና በአገር ጠቅላላ የአገር ምርት (GDP) ውስጥም ከፍተኛ ድርሻ የሚኖራቸው ተቋማት ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ከብቁ የመንግሥት አመራር ጋር፣ **በቻይና ከ 15 ዓመት ባነሰ ጊዜ ውስጥ የሆነው ይኸው ነው**፡፡

የመነሻ ገንዘብ ምንጮች የክልል ም/ቤቶች፣ የሚኒስትሮች ምክር ቤትና የግብርና ሚኒስቴር ሲሆኑ፣ ሥራ ከተጀመረ በኋላ ግን የተተከሉ ወፍጮዎች ገቢዎች፣ የአባላት መዋጮና (ለምሣሌ፣ 2 ብር በወር በቤተሰብ)፣ ከአካባቢው ውጭ የሚኖሩ ተወላጅ ወገኖች ስጦታና በተጓዳኝም የግል ኢንቬስተሮች ይሆናሉ፡፡ መነሻ ሀብቱን የሚያሟላው ግን የፌደራል መንግሥትና የክልል አስተዳደሮች ይሆናሉ፡፡ አጀማመሩና አመራሩ ካማረ በፍጥነት ያድጋል፡፡

### 6.2. የቀበሌ ልማት ድርጅት አደረጃጀት፣ ተግባር፣ ሥልጠናና ቁጥጥር

- <u>የቀበሌ ልማት ድርጅት አደረጃጀት</u>፡- የቀበሌ የልማት ደርጅት አወቃቀር የኩታ-ገጠም ቀበሌዎችን አስተዳደር የሚተካ፣ <u>ለግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎት የተደራጁትን 12,500 የአርሶ-አደር ማሰልጠኛ ማዕከሎችና ማምረቻ ማህበራትን</u> ተጠቅሞ ማሕበራዊውንና ኢኮኖሚያዊውን አላፊነት በሙሉ የሚወስድ፣ በየዓመቱ ግልጽና ነጻ በሆነ ምርጫ 4 አባላት ያሉት አመራር፣

ማለትም የሊቀ መንበር፣ የም/ሊቀ መንበር፣ የፀሐፊና የገንዘብ ያዥ ምርጫ ማድረግና ወጪም ሆነ ገቢ በሊቀ መንበር፣ በም/ሊቀ መንበርና በገንዘብ ያዥ የጋራ ፊርማ ብቻ እንዲፈጸም የሚያደርግ ተቋም ነው፡፡ የም/ሊቀ መንበር ሥራ ሊቀ መንበር በሌለበት ጊዜ ማሕበሩን የሚመራ የአመራር አባል ሲሆን፣ የፀሐፊው ሥራ የስብሰባ ጊዜና አጀንዳ ከሊቀ መንበሩ ጋር ተመካክሮ የማውጣት፣ ስብሰባ የመጥራትና የአመራሩንና የቀበሌ ስብሰባዎችን ውሳኔ መዝግቦ ለቀበሌው ማሳወቅ ነው፡፡ የኦዲት ሥራ  የሚችል ቡድን በዛሬ ወረዳዎች ስለማይገኝ፣ ኦዲት ማስደረግ የዞን አመራር ድርሻ ይሆናል፡፡  በእነዚህ **የቀበሌ ልማት ድርጅቶች**፡-

- የቀበሌውን መጋዘን፣ ወፍጮ፣ ሱቅና የጥገና ማዕከል ዞኑ በአርሶ-አደር ማሠልጠኛው ወስጥ በአማካይ ቦታ ገንብቶ ወጪውን ከ5 ዓመት በኋላ ጀምሮ በ25 ተከታታይ ዓመታት ውስጥ **የቀበሌ ልማት ድርጅት** ይከፍላል፡፡
- በያመቱ መጨረሻ የቀበሌውን የልማት ሂሳብ የዞኑ ኦዲተር አጠናቅቆ ሪፖርት ከተዘጋጀ በኋላ፣ በዞኑ ተወካይና በቀበሌው ልማት ሊቀ መንበር የጋራ ሰብሳቢነት፣ የቀበሌው ሕዝብ የዓመትሥራ ግምገማ በዓል አድርጎ፣ የቀበሌውንም የልማት ዕቅድና ባጀት እንዲያወጣ፣ ለአፈጻጸም ችግሮችም ሁሉ መፍትሔ ሕዝቡ ራሱ እንዲፈልግ ይደረጋል፤ ምርጫም ያካሂዳል፡፡
- አንድ አርሶ-አደር ለአመራር የሚመረጠው ለ 2 ተከታታይ ዓመት ሆኖ፣ ከወጣ ከ 2 ዓመት በኋላ እንደገና ሊመረጥ ይችላል፡፡
- የአመራር አባላት ስብሰባ ቢያንስ በወር ሁለት ጊዜ ይሆናል፡፡ የአመራሩ አባላት ለራሳቸው ስለሚሠሩ አይከፈላቸውም፡፡
- የጥበቃ ሠራተኞችም ከ**ቀበሌ ልማት ድርጅት** አባላት መካከል አመራሩ መልምሎ በባጀቱ መሠረት ይቀጥራል፡፡ አመራሩም ሆነ ጥበቃዎች ለሚያደርጉት ጥፋት በዞኑ ተወካይ ሰብሳቢነት የቀበሌው ሕዝብ አስተማሪና ፈጣን የቅጣት ሥርዓት አውጥቶ፣ የልማት ድርጅቱን የሚጎዳ ጥፋት ሲከሰት በወረዳው ተወካይ ሰብሳቢነት በአጥፊው ላይ የቀበሌው ሕዝብ ቅጣት ይወስናል፡፡
- በያመቱ መጨረሻ፣ ቀበሌዎች በሙሉ ቀደም አድርገው በተስማሙበት ሣይንሣዊ መለኪያ አወዳድሮ፣ ቀበሌዎች ሁሉ የተስማሙበት ሽልማት (ለምሣሌ፣ እንደ ማዳበሪያና ምርጥ ዘር ያለ የልማት ግብዓት በነፃ ወይም በአነስተኛ ዋጋ ያቀርባል፤ የምርት ማጓጓዣ መኪና ይሰጣል፣ ወዘተ) አንደኛ፣ ሁለተኛና ሶስተኛ የሆኑትን **የቀበሌ ልማት ድርጅቶች** ብቻ ዞኑ ይሸልማል፡፡ የሽልማቱ ዓላማ **የዞኑን የቀበሌ ልማት ድርጅቶች** ስኬታማነት **በውድድር** ለማነቃቃት ነው፡፡
- **የተጣራ ትርፍ ክፍፍል፡**- ቀበሌው ሥራ ከጀመረ ከሁለት ዓመት በኋላ፣ ከዓመቱ የተጣራ ትርፍ 10 በመቶ ለወረዳው፣ 5 በመቶው ለዞን፣ 5 በመቶው ለክልል፣ 50 በመቶው ለቀበሌ ልማት (ለጅምር ሥራ ማስፋፊያ፣ ለቤት ግንባታ፣ ለመንገድ፣ ወዘተ.)፣ 30 በመቶው ለማህበሩ አባላት ይከፋፈላል፡፡ <u>**የማህበር አባላት ድርሻ 30 በመቶ መሆኑ ያተጋቸዋል በማለት ነው፡፡**</u>

- **የቀበሌ ልማት ድርጅት ተግባር**፡- በዞኑ ድጋፍ፣ የግብርና ግባቶችን ማከፋፈልን (**ፉጉሎ የአኩሪ አተር፣ የኑግና የሌሎች የምግብ ዘይት ፋብሪካዎች ጭማቂ ነው፡፡  በከብት መኖነቱ ላይ አፍላቶክሲን ቢታይበትም ከፉጉሎ የናይትሮጅን ማዳበሪያም በመቀመም ከአሞኒያ ፎስፌት የተቀመመውን ማዳበሪያ ግዢ የቀነሱ አገሮች አሉ፡፡  የግብርና ምርምር ተቋም ፉጉሎን በማዳበሪያ፣ በመኖነትና በሌላም ለመጠቀምና በአገር-በቀል የአንበጣና ሌላም ተባይ መድሐኒት ጥናት ቢያደርግ ይጠቅማል፡፡** ) ፤ ምርት ለገበያ ማቅረብን፤ የግብርና መሣሪያዎችን በድጎማ በመግዛት፣ የአገልግሎት ክፍያውንና የአገልግሎቱን ተራ በአባላት ስምምነት ወስኖ፣ የግብርና መሣሪያዎችን አገልግሎት ለሁሉም አርሶ-አደር በፕሮግራም ማዳረስን፤ ሱቆችን ማሟላትን ፤ የሰውና የዕቃ ጋሪ መፈብረክን፤ የግብርና መሣሪያ፣ ወፍጮና ጋሪ ጥገና ማዕከል ማስተዳደርን ይጨምራል፡፡ ዘመናዊ የባህላዊ ዕደ ጥበብ  (ሽመና፣ ብረትና ጌጣጌጥ ሥራ፣ ሸክላ ሥራ፣ ቆዳ ሥራ፣ ሰፌት፣ ባልትና) ሥራዎችን ያበረታታል፡፡  <u>**የተመናመነ ደን ያለማል፤ የውሀ ሀብት ጥበቃና ቆጣቢ አጠቃቀም**</u> በዞኑ ድጋፍ ያከናውናል፡፡

  መንደሮችን በፈረስ፣ አህያ ወይም በግመል የሚጎተቱ የዕቃና የሰው ማጓጓዣ ጋሪዎች በሚያስሄዱ የመንደር መንገዶች ያገናኛል፡፡ የጋራ ሃብቱንና ገቢውን ያስተዳድራል፡፡ ልማት በቀበሌው ምርትና አቅም መሠረት ያከናውናል፡፡ የግብርና መሣሪያ ዋጋ፣ ጥገናና ማሰቀመጫውም ከከብቶቹ ጋር በሚጋራት ጎጆ የሚኖር አርሶ-አደር አቅም ስለማይቻል፣ የግብርና ሚኒስቴርን የእርሻ ሜካናይዜሽን ዕቅድ ለማሳካት መሣሪያው በቀበሌ ልማት ድርጅቱ ባለቤትነት ሥር ሆኖ የጥገና አገልግለቱ በማዕከሉ ይመራል፡፡ <u>**ባጠቃላይ፣ ድርጅቱ ልማዳዊ አሠራርን በዕድገት-መር አሠራር ይተካል**</u>፡፡

- **የቀበሌ ልማት ድርጅት ሥልጠና**፡- ተግባር-ተኮር ሥልጠና በሂሳብ አያያዝ፣ በአናጢና ብረታ ብረት ሥራ፣ በወፍጮና በግብርና መሣሪያ ጥገናና በንግድ አስተዳደር መሰጠት ያስፈልጋል፡፡ ምናልባት ለወረዳው ወይም ለዞኑ በሙሉ አንድ ማሠልጠኛ ማዕከል ያሻ ይሆናል፡፡

- **በዞን ዋና ከተማ የምርት ግበዓትና መሸጫ መደብር መገንባትና የትርፍ ክፍፍል፡-** በዞኑ ከተማ መደብር ገንብቶ ለዞኑ ወረዳዎች የምርት ግባቶች  የሚያከፋፍልበት፣ ከዞኑ ቀበሌዎች የሚመጣውን ምርት ከደላላ ነፃ በሆነና የአምራቹን ወጪ አገናዝቦ ከየቀበሌው የልማት ድርጅት ጋር <u>በግልጽ ውይይት በጋራ አነስተኛውን መሸጫ ዋጋ ወስኖ</u>፣ ምርታመነትን የሚያበረታታ ዋጋ ለአምራቹ ከፍሎ ወደ ዞን ከተማ ማምጣትና ለአገር-አቀፍ ገበያ በማቅረብ፣ ከሚያገኘው የተጣራ ትርፍ ውስጥ 5 በመቶውን ለክልሉ ፈሰስ አድርጎ፣ 5 በመቶውን ለራሱ አስቀርቶ፣ 5 በመቶውን ለወረዳ አስተዳደር ሰጥቶ ፣ 85 በመቶውን መልሶ ለቀበሌ ልማት ድርጅቶች ልማት (ለፋብሪካ፣ ለጥገና ወርክሾፕ፣ ለመደብር፣ ወዘተ) ማጠናከሪያ እንዲሆን የልማት ድርጅቶች ባቀረቡት ምርት ጠቅላለ ዋጋ ልክ ለእየቀበሌ ልማት ድርጅቶች ያከፋፍላል፡፡  <u>**ይህን በሀቅ መፈጸም የሚችል የዞን አመራር መኖርና አመራሩንም በጥብቅ የሚቆጣጠር የክልል አመራር መፍጠር አንዱ የገጠር ኢንዱስትሪ ልማት የስኬት ቅድመ-ሁኔታ ነው፡፡**</u>  ይህ የዞን መደብርም በያመቱ በዞኑ አመራር ቁጥጥር ኦዲት ተደርጎ ሪፖርቱ ለቀበሌዎች ይላካል፡፡ ክልሉ ዞኖችን ይቆጣጠራል፣ ባጥፊ ላይ ፈጣን እርምጃ ይወስዳል።

- የቀበሌ ልማት ድርጅቱ ለክልሉ ታክስ ይከፈላል፡፡ ነገር ግን የእነዚህን ለጋ የልማት ድርጅቶች ዕድገት ለማበረታት፣ ክልሉ የተለየ የታክስ ሥርዓት ያወጣል፡፡ <u>**የአርሶ-አደሩና አርብቶ አደሩ ገቢ ካደገ፣ እያደረና በተከታታይ የክልሉ መንግሥት የዓመት ገቢም እያደገ ይሄዳል**</u>፡፡

- ይህ የቀበሌ ልማት ድርጅት የወረዳ መንገድና ሙብራት ባላቸውና ምሣሌ በሚሆኑ **<u>ብቁ አመራር ባላቸው ወረዳዎችና የወረዳ ቀበሌዎች ተጀምሮ</u>**፣ አፈጻጸሙን እያሻሻሉ ተፋጥኖ ዞን-አቀፍ እንዲሆን የልማት መሠረተ-ልማቶችን ማሟላትና ልማቱን ማዳረስ የእያንዳንዱ ዞን ተቀዳሚ ተግባር ይሆናል፡ክልሉ የዞን አመራሮችን የሚያወዳድርበትና የሚገመግምበት ከሁሉም ወገናዊነት ችግር የጸዳ ሣይንሣዊ የመገምገሚያ መለኪያ ያወጣል፡፡ የክልሉንም አመራር ከሌሎች ክልሎች ስኬት ጋር በማወዳደር ይገመገምበታል፡፡ በኋላ-ቀርነት የማይቆጭ አመራር መሾም የለበትም፡፡
- የዞኑ አስተዳደር በያመቱ የቀበሌውን ልማት ድርጅት ሂሳብ ኦዲት ያስደርጋል፡፡

- **ጠቅላላ ቁጥጥሩ** በዞኑ አመራር የቅርብ ክትትል ተጀምሮ፣ በክልሉ ምክር ቤት/ርዕሰ-መስተዳድር ተጠናክሮ፣ በፌደራል የግብርና ሚኒስቴር ተቀናጅቶ፣ ዋናዎቹ የገጠር ልማት ባለቤቶች፣ የአገርን ልማት የሚመሩት የክልሉ ም/ቤት/ ርዕሰ መስተዳድርና የሚኒስትሮች ምክር ቤት ሊሆኑ ይገባል፡፡ **<u>ከሕዝባችን ቢያንስ የ80 በመቶውን ሕዝብና የኢኮኖሚ መሠረት የሆነውን ክፍል ልማት መምራት የአገር ልማት መምራት ስለሆነ፣ የአገርን ሰላም ያለምንም ቅድመ-ሁኔታና ለዘብተኛነት አረጋግጦ፣ የገጠርን ልማት ማሳካት የክልል ም/ቤትና የሚኒስትሮች ም/ቤቶች ተቀዳሚ ተግባር ነው</u>**፡፡ ሕዝብ መንግሥትን ብቸኛው ኃያል የታጠቀ ኃይል ለማድረግ ከዕለት ጉርሱ ቀንሶ ብዙ ወጪ በመደብ ባግባቡ ያስታጠቀው፣ የአገርን ሰላምና ዕድገት በማስጠበቅ ረገድ ምን ጊዜም ሆነ የትም ቦታ፣ ከሕገ-ወጦች ጋር ያለምንም ድርድር ፈጣን እርምጃ እንዲወስድ ለማስቻል ነው፡፡ ስለሆነም፣ የሕገ-መንግሥታዊ መብቶች መከበር ለልማትና ዕድገት ቅድመ-ሁኔታ በመሆኑ፣ የመብቶቹ መከበር ከማንም ጋር በምንም ወቅት ለድርድር አይቀርብም፡፡

- ቀበሌው ተከስሶ የሕግ ባለሙያ ድጋፍ ሲያስፈልግ፣ ዞኑ ለቀበሌ ልማት ደርጅት ጠበቃ ያቆማል፡፡

ይህ የቀበሌ ልማት ድርጅት አደረጃጀት፣ ተግባርና የወጣቶች ሥልጠና **<u>ሰፊ ልምድና የተሻለ አካባቢያዊ ዕውቀት ባላቸው አርሶ-አደሮች ምክር ሊዳብር የሚችል ነው</u>**፡፡ የድርጅቱ ባለቤት፣ ከመንግሥት የቅርብ እገዛ ጋር፣ ምንጊዜም ሕብረተሰቡ መሆኑ ሊለወጥ አይገባም፡፡ ***መንግሥት የለማውን ያለምንም ካሳ መውረስና መሸጥ እንጂ በብቃት መነገድና ልማት መምራት እንደማይችል*** (*ከኢትዮጵያ አየር መንገድ ውጭ*) ***ባለፉት 45 ዓመታት ታይቷል፡፡***

## 7. የገጠር ልማት ማስፋፊያ ምክረ-ሃሳብ ማጠቃለያ

ከቻይና ጋር ንጽጽሩ ያለአቻ መንጠራራት ቢሆንም፣ የኢትዮጵያና የቻይና የተፈጥሮ ሃብት ገጽታ [4] እንደሚከተለው ነው፡-

| **የገጽታ ዓይነት** | **ኢትዮጵያ** | **ቻይና** | **የቻይና ገጽታ በኢትዮጵያ ሕዝብ ብዛት ልክ ቢመጠን** |
|---|---|---|---|
| የሕዝብ ብዛት *(እአአ 2017 ለቻይና)* | 102,000,000 | 1,379,000,000 | 102,000,000 |
| ከጠቅላላው ሕዝብ የገጠር ሕዝብ በመቶ *(እአአ 2017 ለቻይና)* | 80 | 43 | 43 |
| የአገር ስፋት (1000 ሄክታር) | 110,430 | 960,000 | 71,008 |
| የደረቅ መሬት ስፋት *(1000 ሄክታር)* | 100,000 | 942,470 | 69,711 |
| በግብርና ላይ የዋለ መሬት ስፋት*(1000 ሄክታር)* | 36,259 | 515,358 | 38,119 |
| ውሀ ያለበት ከጠቅላላው በመቶ | 0.7 | 2.8 | 0.028 |

የመጨረሻው ሰንጠረዥ ተራሮችዋ፣ ሸለቆዎቿ፣ ውሀዎቿና የእርሻ መሬቶቿም በኢትዮጵያ ሕዝብ ልክ ቢመጠኑ፣ የቻይናን እአአ የ2017 የተፈጥሮ ሀብት የሚያሳይ ነው፣ የመጀመሪያው ሰንጠረዥ የኢትዮጵያን የ2007 ዓ ም ገጽታ ያሳያል፡፡ እአአ በ2015 በግብርና ሥራ ላይ የዋለው መሬት ልክ ላይ ካለው የ2017 መሬት ብዙ አይለይም በሚል እሳቤ፣ ቻይና እአአ በ2015 ያመረተችው የእህል ሰብል 621.44 ቢሊዮን ኪሎ ነበር፡፡ የኢትዮጵያ የ2007 የምርት ዘመን ምርት 270.4 ሚሊዮን ኩንታል ነበር፡፡ ይህ ንጽጽር ሙሉ በሙሉ ተገቢ ነው ባይባልም፣ የኢትዮጵያ ምርታማነት ከቻይና ምን ያህል እንደራቀ ይጠቁማል፡፡

በዚህ ላይ፣ ሠንጠረዡ ከቻይና የተሻለ የውሀ ሀብት ኢትዮጵያ እንዳላት፣ የግብርና መሬቷን ግን ገና የቻይናን ያህል እንዳልተጠቀመችበት ይጠቁማል፡፡ ስለሆነም፣ የወቅቱ የምርት ዕጥረት፣ የዋጋ ግሽበትና የውጭ ምንዛሪ ችግራችን በአንድ በኩል የብዙሀኑ የግብርና መሣሪያ ባለፉት 2000 ዓመታት ባለመለወጡም ጭምር (**ምናልባት የአሜሪካን የግብርና መሣሪያ በሜካናይዜሽን ስም በድሀ አርሶ-አደር ላይ ለመጫን ተሞክሮ ይሆናል።**) የእኛ የግብርና ምርታማነት የቻይናን ሲሶ አካባቢ በመሆኑ፣ በሌላ በኩል **በለም መሬታችንና በሰፊ የውሀ ሃብታችን ባግባቡ ባለመጠቀማችንና የገበያ ሥርዓቱንም ባለማስተካከላችን የመጣ ይመስላል፡፡**

በኢትዮጵያ ከገጠር ቤተሰቦች 98 በመቶ በእርሻ ላይ፣ ከትናንሽ ከተሞችም ሕዝብ 42 በመቶ እንዲሁ በእርሻ ላይ የተሰማራ ነው ቢባልና ከአገሪቱ ጠቅላላ ምርት (GDP) 35 በመቶ አካባቢ፣ ከወጪ ንግድ 80 በመቶ አካባቢ፣ ከአገሪቱ ሠራተኞችም 80 በመቶ አካባቢ፣ ከውጭ ምንዛሪ ግኝት ቢያንስ 80 በመቶ የእርሻው ዘርፍ ውጤት ሆኖ፣ ከሕዝባችንም የ85 በመቶው አካባቢ መኖሪያ ሆኖ ሳለ፣ የግብርናው ዘርፍ ባጀት ከህዝቡ ብዛትና ከኢኮኖሚ ዋልታነቱ ጋር የተመጣጠነ ሆኖ አይታይም፡፡ ለተሻለ የግብርና ውጤት ለመብቃት፣ በመጀመሪያ እንደ 1996-2005 ዘመናት፣ ባጀቱ ወደ 15 በመቶ አካባቢ አድጎ፣ **<u>የገጠር ልማትም በሚኒስትሮች ም/ቤትና በክልል ም/ቤቶች</u>** የተለየ ትኩረት ሊያገኝ ይገባል፡፡ **<u>በተከታታይ ዓመታት ለሚራብ ጀግና ሕዝብና ለታሪካዊት አገራችን ክብር፣ ለኢኮኖሚ ዕድገታችንና ለሰላምም፣ መንግሥት ድህነትን</u> ለዘመናት ተላምዶ ቸጋርን ተሸክሞ መንገዳገድ አስከፊና ለሉዓላዊነታችንም መከበር በጣም አደገኛ ነው፡፡**

ኢትዮጵያና ቻይና በፊውዳል ሥርዓትና በአንድ ዓይነት ፓርቲ አገዛዝ ውስጥ አልፈው ሁለቱም ፌደራል-መሰል መንግሥታዊ አወቃቀር ቢኖራቸውም፣ በተለይ ቻይና እአአ ከ1978 ጀምሮ ያደረገችው ታምራዊ የኢኮኖሚ ዕድገት፣ በኢትዮጵያ ተገኘ ከሚባለው ስኬት በብዙ መንገድ ይልቃል፡፡ ቻይና ከ1980ዎች ጀምሮ አርሶ-አደሩን ወደ ገበያ-መር ኢኮኖሚና ወደ ትላልቅ የልማት ድርጅት (ENTERPRISE) ባለቤትነትና ስታሸጋግር፣ የኢትዮጵያ አርሶ-አደር ግን ከሞላ ጎደል ለዘመናት በነበረው ጥንታዊ አስተራረስ ተወስኖ በመቀጠሉና የተቀናጀ ዘመናዊ ቴክኖሎጂ ሙሉ ተጠቃሚ ባለመሆኑ፣ ዛሬም በግብርና ኤክስቴንሽን ጥረት መጠነኛ መነቃቃት ቢፈጠርም፣ በኋላ-ቀር የግብርና መሣሪያ ታስሮ፣ የተሟላ ዘመናዊ የምርትና ቴክኖሎጂ ግባት፣ የአዝመራ ጥበቃ፣ የሰብል አሰባሰብ፣ የጎተራና **<u>የገበያ ትሥሥር ድጋፍ ባለማግኘቱ</u>**፣ 30 ሚሊዮን የሚገመት ወገናችን፣ ከጠቅላላ ወገናችን ሲሶው አካባቢ፣ ከድህነት ወለል በታች ሲሆን፣ በቻይና ግን በተመሳሳይ የድህነት ደረጃ ላይ ያለው 30 ሚሊዮን አካባቢ ሆኖ ከሕዝቡ 2 በመቶ በታች ነው፡፡ ይህ የገጠር ድህነት ከፊል መንስኤው የግብርና መሣሪያ ኋላ-ቀርነት፣ የዘመናት ደን ጭፍጨፋ፣ የአፈር መሸርሸር፣ የምንጭ መድረቅ፣ የመሬት መጣበብ፣ የምርታማነት ደካማነት ሲሆን፣ የመጋቢ መንገድና የመሬት ባለቤትነት አለመኖርና የአመራር ድክመት ተደራቢ ችግሮች ናቸው።

የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ ከ ADLI ወደ መሰሉ PASDEP፣ ከዚያም ወደ GTP 1 እና GTP 2 በማሸጋገር መጠነኛ የኢኮኖሚ ዕድገት ቢመጣም፣ ዕድገቱ በአመዛኙ መንግሥት-መርና ከተማ-ተኮር ስለነበር፣ በአርሶ-አደሩና አርብቶ-አደሩ ገቢ ላይ በግልጽ የሚታይ ለውጥ አልታየም፡፡ የአርሶ-አደሩንና የአርብቶ-አደሩን ዓመታዊ ገቢ ለውጥ የሚያሳይ የመንግሥት ጥናትም አልተገኘም፡፡ ዛሬም፣ አርሶ-አደሩ ከሞፈርና ቀንበሩና የ2000 ዓመት በፊት ማረሻ፣ ሴት አርሶ-አደር ከቅምባና ማድጋ ሸክምና ከዱር እንጨት በጀርባ ተሸክሞ ከማምጣት አልተላቀቁም፡፡

በአውሮጳ፣ በአሜሪካና በእስያም እንደተደረገው፣ ለዕድገቱ ተመጣጣኝ የሆነ ቴክኖሎጂ ማምጣቱና በስፋት የመደጎሙ ወግ ይቅርባቸውና፣ የአገሪቱን የምግብ ዋስትና ለማረጋገጥ በምርጥ ዘርና ማዳበሪያ ግባት አቅርቦትና በግብርና መሣሪያ ድጎማ፣ ምርቱንም ወደ ገበያ ለማውጣት ድጋፍ እንዲሰጠው **<u>በየጊዜው የባላገሩ አስከፊ የችጋር ኑሮና የድህነቱ ጨካኝነት ቢጠቁሙም</u>**፣ ለአገዛዙ አጋር ነበረ ለሚባልለት ድሀው አርሶ-አደርና አርብቶ-አደር ቀጥተኛና ጠንካራ ድገፍ ለመስጠት በመንግሥት የተደረገ ሙከራ ስለመኖሩ መረጃ የለም፡፡

**<u>የኋላ-ቀርነታችንም አንዱም ምክንያት፣ ልክ እንደ ግብርና መሣሪያው ጥንታዊነት፣ የትምህርት ጥራትና ይዘትም ለ45 ዓመታት ወደ ጎን ተገፍቶ፣ የአብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ መኖሪያና የአገር ሉዓላዊነት ብቸኛ ዋስትናና የኢኮኖሚውም መሠረት የሆነው ገጠር ከሞላ ጎደል ለዘመናት ተረስቶ፣ ጠቅላላ ሕልውናው በገጠሩ ላይ ጥገኛ ለሆነው በአናሳው ከተሜ አካባቢ ላይ ላይ መቀባባት ቅድሚያ መሰጠቱ ነው</u>**፡፡ ዓላማ-ተኮር ያልሆነ ትምህርትና ያለ ግብርና ዕድገት የኢትዮጵያ ብልፅግናና ሉአዓላዊነት መረጋገጥ አይችሉም።

የማህበራዊ ጥበብ ባለሙያዎች የድህነትን አመጣጥ በ 3 ይመድቡታል፦ **አንደኛው በደካማ የኢኮኖሚ ሥርዓት ምክንያት የሚመጣ፣ ሁለተኛው በአካባቢ መራቆት የሚመጣና ሶስተኛው ከማሕበራዊና ባህላዊ ማነቆዎች የሚመጣ ነው ይላሉ**፡፡ ደካማው የኢኮኖሚ ሥርዓት ቢስተካከል ሌሎችን መቅረፍ ይቻላል፡፡ ስለሆነም፣ ደካማ ሥርዓት አንድን አገር እግር ከወርች ጠፍሮ ከያዘ፣ ይህ ችግር ያለበት አገር ዕጣ ፈንታው በድህነት ሥር ለዘመናት መማቀቅ ነው፡፡ የዛሬው የክልሎች የግብርና መሬት ይዞታ [11]፣ ቀጥሎ እንደሚታየው፣ የደካማ ፖለቲካና ኢኮኖሚ ሥርዓት ነፀብራቅ ነው፡፡

| ክልል | አማካይ የቤተሰብ ይዞታ (ሄክታር) | 0.5 ሄክታርና በታች ያላቸው ቤተሰቦች *(ከመቶ)* |
|---|---|---|
| ደቡብ | 0.46 | 57 |
| ኦሮሚያ | 1.21 | 25 |
| አማራ | 1.08 | 28 |
| ትግራይ | 0.97 | |
| **ኢትዮጵያ** | **0.95** | **35** |

በዛሬው ምርታማነት ደረጃ፣ ከ 12 ሚሊዮን ያህሉ አርሶአደር ቤተሰቦች መካከል፣ በአንድ በኩል ሰፋፊ ለም መሬት ለኢንቬስተር ይሰጥ የሚል ወጤት-የለሽ የመንግሥት መርህ ባለበት፣ በሌላ በኩል የግብርና መሬት የጠበባቸውና ከግማሽ ሄክታር በታች ያላቸው 4 ሚሊዮን *(35 በመቶ)* የሚገመቱ በረሀብ አፋፍ ላይ ናቸው፡፡ ብዙ አገሮች ይህን ችግር የተቋቋሙት አንድም መሬት ለጠበባቸው መሬት ከበቂ ድጋፍ ጋር በማደል፣ በተጨማሪም ሥራ-አጥ ለሆነው የገጠር ቤተሰብ የአገልግሎትና የኢንዱስትሪ ዘርፎችን በገጠር በመክፈት የሥራ ዕድል በመፍጠር ነው፡፡

ይህን ዓይነት የገጠር ልማት አፋጥኖ አለማጠናከር፣ በጎ ለማይመኙልን ኃይሎች የማያባራ የገጠር ትርምስ መድረክ ማመቻቸት ነው፡፡ እስከ ተወሰነ ደረጃ፣ እርሻውን በማዘመንና ምርታማነትን በማሳደግ፣ በሰብል አያያዝ፣ በአጨዳ፣ አዝመራ በመሰብሰብ መጠነኛ ተጨማሪ የሥራ ዕድል መፍጠር ይቻላል፡፡ ሌላው ዘዴ መንግሥት ከግብርናው የበለጠ ድጋፍ እየሰጠ በማደፋፈር ላይ ያለውን የከተማ አካባቢ ኢንዱስትሪ ፓርክ ዕድገት **<u>አገር-ተኮር</u>** ማድረግ ነው፡፡ አሁንም ሌላው ዘዴ፣ አገሬውን የልማት አጋር ይበልጥ ማነቃቃት ነው፡፡ በእነዚህ ዘዴዎች ላይ ለገጠሩ ወጣት ማስማሪያ፣ ላይ እንደተመለከተው፣ የገጠር አገልግሎትና ኢንዱስትሪ ግንባታ መጀመር ነው፡፡

ቻይናና ሌሎችም የለሙ አገሮች እንዳደረጉት፣ በአንድ በኩል ግብርናውን አጠናክሮ ደግፎ ገበያውንም ማዘመን፣ በሌላ በኩል የልማት አጋር ዜጋን ማጠናከርና የገጠር ኢንዱስትሪ ተቋማትንም በማቋቋም፣ መሬት ለጠበባቸው አርሶ-አደሮችና ለገጠር መሬት-የለሽ ወጣቶች ተጨማሪ የሥራ ዕድል መክፈት አስፈላጊ ነው፡፡ በአፍሪቃም ደረጃ፣ የኢትዮጵያ የገጠር

ተቋማት የኢኮኖሚ ድርሻ ከብዙ አገሮች ያንሳል [13]፡፡ ግብርናውን ማጠናከርና የገጠር ልማት ተቋማትን አስፋፍቶ ድህነትን መቀነስ፣ የአገር ክብርና የሕልውና ጉዳይም ስለሆነ፣ ያለጠንካራ ግብርና ኢንዱትሪ መገንባትም ስለሚያዳግት፣ <u>**ግብርናን የመንግሥት ተቀዳሚ ተግባር ማድረግ ያሻል**</u>፡፡ ዛሬም፣ <u>**በቻይና ግብርና የገገሪው ፓርቲ ማዕከላዊ ኮሚቲ ተግባር ነው**</u>፡፡ ስኬቱም ዓለምን ያስደነቀ ሆኗል፡፡

ከላይ የቀረቡትን ሃሳቦች ለማጠቃለል፣ *የክልል ም/ቤቶችና የሚኒስትሮች ም/ቤት፣ ቢቻል በመቀናጀት፡-*

*(ሀ) ለአርሶ-አደሩና አርብቶ-አደሩ ብቁ የማምረትና የገበያ ትሥሥር ድጋፍ ለመስጠት፣ በግብርና ሚኒስቴር የ2012 ዕቅድ [1] የታለመውን 21 በመቶ የዕድገት ግብ ዓይነት ለማሳካት፣ የግብርናን የፌደራል ባጀት አአአ በ2003 የአፍሪቃ መንግሥታት በማፑቶ ጉባዔው የግብርና ባጀቱ ድርሻ ከ10 በመቶ እንዳያንስ በተስማማው መሠረት፣ ከዛሬው 3.75 በመቶ ወደ 1996-2005 15 በመቶ አካባቢ ከፍ ማድረግ ይገባል፡፡ የግብርና ሚኒስቴር በ2012 የምርት ዘመን አምስት ሰብሎች ብቻ መርጦ ለኩታ-ገጠም ሙከራ በተወሰኑ ወረዳዎች ላይ ማቀዱና የቆላ ስንዴም ማስፋፋት ሥራ በአፋር፣ ደቡብና ሶማሌ ክልል ብቻ መወሰኑ መነሻው የባጀት ዕጥረት ሳይሆን አልቀረም፡፡ <u>**የዛሬው የግብርና ባጀት በዛሬ 10 ዓመት ብር ቢለካ፣ መጠኑ ከዛሬ 10 ዓመት ባጀት ግማሽ በታች ነው**</u>፡፡ በተጨማሪ፣ ግብርናን ለማዘመን፣ ከምርጥ ዘርና ማዳበሪያ አቅርቦትና የገበያ ትሥሥር ከማመቻቸት ሌላ፣ **ለድሀ አርሶ-አደሩ የሚመጥን መከስከሻ፣ መዝሪያ፣ ማጨጃ፣ መውቂያ፣ የእጅ የተባይ መርጫ መሣሪያዎችንና ከፋጉሎና ከሌላም የተቀመመ ማዳበሪያና መኖ** ለማምረትና ለቀበሌ ልማት ድርጅቶች በድጐማ ለማደል፣ አገር-በቀል መኖዎችን፣ ማዳበሪያዎችንና እርካሽ መሣሪያ <u>**ማምረቻዎችን በአስቸኳይ መገንባት**</u> ይበጃል፡፡ **የልማዳዊዊ አሠራር ውጤት ድህነትን በመንከባከብ ሉዓላዊነትን የማስከበር ዓቅም ማጣት ነው።***

*(ለ) የዛሬው የግብርና ልማት ዋና ሥልት ገበያ-ተኮር ነው ይባል እንጂ፣ ብዙ ብክነት በተዘገበበት በምርት አሰባበሰብ ላይ፣ በጎተራ ሥራ፣ በእህል ከምችት አያያዝ፣ ምርቱን ከገበያ ጋር ለማስተሳሰርና ዋጋን በማረጋጋት ላይ በቂ አልተሠራም፡፡ በ2011 የምርት ዘመን ከቦረና እስከ ጎንደር ያለው አርሶ-አደርና አርብቶ-አደር ምርቱን ለደላላ ለማስረከብ መገደዱን ደጋግሞ አመልክቷል፡፡ ነገር ግን የተቀናጀ ድጋፍ ሲሰጥ አልታየም፡፡ <u>**የክልል አስተዳደርና የፌደራል መንግሥት የገበያ ትሥሥሩን የማረጋገጥና ዋጋም የማረጋጋት አቅም አላቸው**</u>፡፡*

*በለም መሬታችን፣ በሰፊው የውሀ ሀብታችንና በታታሪው አርሶ-አደር ወገናችን <u>**በወራት ውስጥ ሊበቅል የሚችል ስንዴ ከውጭ በቢሊዮን ብር በተከታታይ ዓመታት የምንገዛው የድሀው አርሶ-አደር ማነቃቂያ ድጋፍና የመንግሥት የቅርብ ትኩረትና ቅንጅት በማነሳቸው ነው**</u>፡፡ **አስከፊ ድህነትን ተሸክሞና የዕድገት ዕድልን በመናቁር፣ በስንፍናና በየዋህነት በተከታታይ ዘመናት እያባከኑ፣ በቶክራና በሰብሰባ ጋጋታ ብቻ የጠላትን ድፍረትና ተንኮል መቋቋም ከባድ ነው፡፡** ጃፓን ዕድገቷን በ19ኛው ክፍለ ዘመን በቁጭት በራሷ ልጆች ያፋጠነችው የውጭ ተፅዕኖና የወረራ አደጋ ለመቋቋም ብቸኛው አስተማማኝ ዘዴ በመሆኑ ነው፡፡*

*የምሥራቅ እሲያ ድሀ አገሮች <u>**ከ 30 ዓመት ባነሰ ጊዜ ከከበርቴ አገሮች መደብ መግባታቸውን እያየን፣**</u> እኛ ግን የዕድገት ማነቆ ነበር የተባለለትን ንጉሣዊ ሥርዓት አስወገድን ከተባለ ከ 45 ዓመት በኋላም በባሰ ድህነት ውስጥ ለመዳከር ያበቃንን ኋላ-ቀርና የነቀዘ አሠራር ማስተካከል አቅቶናል፡፡ ለዘመናት በድህነት መዳከር፣ የጠላትን ንቀት ይጋብዛል፣ ከዚያም አልፎ ትንኮሳ ይከተላል፡፡ መቅደላን፣ ኩፊትን፣ ጉርዐን፣ ጉንደትን፣ ዶጋሊን፣ ሰሐጢን፣ መተማን፣ አመባላጌን፣ መቀሌን፣ አድዋን፣ ማይጨውንና የቅርቡን የካራማራንም ወረራ ማስታወስ ይጠቅማል፡፡ ድሀና ደካማ ናቸው ብለው ባይገምቱ ኖሮ የ19ኛው ክፍለ ዘመንና የ20ኛው ክፍል ዘመን ወራሪዎቻችን አይደፍሩንም ነበር፡፡ ስለዚህ፣ <u>**በዋናነት ለመደፈር ያበቃንን አስከፊ ድህነት ለማስወገድ፣ ለብዙሀኑ የገጠር ወገናችን የሚመጥን ድጋፍ፣ ባጀትና ብቁና ትጉ አመራርና ሠራተኛ መድበን፣ በከፍተኛ የመንግሥት አካላት ያላሰለሰ ክትትልና ግምገማ እየተደረገ የነደለውን ፈጥኖ በማስተካከል፣ የገጠር ድህነትን ለፋጥነን መዋጋት አንዱ ተቀዳሚው የመንግሥት ተግባር ነው**</u>፡፡ ይህን ለማድረግ፣ ግብርናና ትምሕርት በምስጉንና አገር-ወዳድ ባለሙያዎች መመራት አለባቸው።*

*(ሐ) የግብርና ዘርፍ የሰብል ምርታማነት እንደ ለሙ አገሮች መሆኑ ቀርቶ፣ የኢትዮጵያ የ2012 የሰብል ምርታማነት በሄክታር የቻይናንና የሌሎች አገሮችን ግማሽ እንዲጠጋ ግብርና ሚኒስቴር አቅዷል [1]፡፡ ይህንንም ለማሳካት፣ የግብርና መሣሪያውን፣ የአካባቢ ጥበቃውን፣ ምርምሩን፣ የግባት አቅርቦቱንና የአገልግሎቱን ጥራት ማሻሻል፣ የኤክስቴንሽናችንንም **ለየመሬቱ ተስማሚ የግባት ዓይነትና መጠን አስተካክሎ የማማከር አቅም** ማሳደግ ያሻል፡፡ በተለየየ መንገድ ማዳበሪያ አምርቶና ከውጭ ማዳበሪያ ጋር ጥቅምና ጉዳቱን አወዳድሮ የሚያዋጣ ሲሆን መጠቀምም ወጪ ይቀንሳል፡፡*

*<u>**ባይለመድም፣ ሕዝብ በስፋትና በመሠረታዊነት ለተቸገረባቸው ለስንዴ፣ ጤፍ፣ ጥራ-ጥሬ፣ በቆሎ፣ በርበሬና ቅመማ-ቅመም**</u> **አምራቾች በምርታማነት ላይ ተመስርቶ ድጎማ በመስጠት፣ ከሸማቾች ማሕበር ጋር አቀናጅቶና ድጎማውን በማከል የሚያበረታታ የዋጋ ስምምነት እንዲደረግ አመቻችቶ፣ አስተማማኝ የዋጋ ቁጥጥር ሥርዓት በመዘርጋት የምርትን ጥራትና ዕድገት ማነቃቃትና የዋጋ ውድነትን ማቃለል ይቻላል፡፡***

*<u>**ለምሣሌ**</u>**፣** <u>**የኩንታል ቀይ ጤፍ**</u> አገር-ቀፍ አማካይ የማምረቻ ዋጋ 1200 ብር በሄክታር ቢሆን፣ **1ኛ**/ ምርታማነቱ ከ30 ኩንታል በሄክታር በላይ ከሆነ፣ የአርሶ-አደሩ መሸጫ ዋጋ፣ ከድጎማ ጋር፣ የማምረቻው 50 በመቶ ተጨምሮበት ለሸማች ማኅበራት መሸጫው **1800 ብር** በኩንታል ቢሆን፣ **2ኛ**/ ምርታማነት 30 ኩንታልና ከዚያም በታችና እስከ 25 ኩንታል ከሆነ፣ መሸጫ ዋጋው የማምረቻው 45 በመቶ ተጨምሮበት በእርሻው ላይ ለሸማች ማኅበራት መሸጫው **1740 ብር** ቢሆን፣ **3ኛ**/ ምርታማነት ከ25 ኩንታል በሄክታር በታች ከሆነ፣ ከደላላ ዋጋ በላይ፣ ግን ከ **1740 ብር** በታች (ለምሣሌ **1700 ብር**) ቢከፈል አርሶ-አደሩን ያበረታታል፡፡ የሸማች ማህበራት ለሸማቹ መሸጫ ዋጋ ከ **1750 ብር** **[(1/3) x (1700 + 1740 + 1800) ≈ 1747]** እንዳይበልጥ መገደብና አፈጻጸሙን መቆጣጠር ያሻል፡፡ በእያንዳንዱ ሸማች ማኅበር የሚከሰት <u>**ሕጋዊ ኪሳራ**</u> ካለ መንግሥት በድጎማ መልክ ለማህበሩ ይከፍላል፡፡ ይህ የአምራቹና የከተሜው ድጎማ የምርት ዕድገት አነቃቅቶ፣ የከተሜውን የኑሮ ውድነት አርሮ ቀንሶ፣ የዋጋ ግሽበትን ገርቶና የውጭ ምንዛሪን ዕድገት አለምልሞ፣ መንግሥት ከውጭ ገዝቶ ከሚደጉመው ያነሰና የውጭ ምንዛሪም ቆጣቢ ይሆናል፡፡*

*የዋጋው አወሳሰን ዓላማ አንድም አርሶ-አደሩ ለምርት ካወጣው ወጪ በታች እንዳይከፈለው ለመከላከል፣ ሁለተኛ የላቡ ዋጋ በንግድ ሥራ ከተሰማሩ ወገኖች ጋር ተቀራራቢ እንዲሆንና፣ ሶስተኛም የተሻለ ምርታማነትን ለመሸለምና ለማበረታታት ነው፡፡ ይህ አሠራር በአማካይ የአካባቢ የማምረቻ ዋጋ ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ ይህን ዋጋ የኤክስቴንሽን አገልግሎቱ የልማት ወኪል (Development Agent)ማወቅ አለበት፣ ሲጀመር ካላወቀ ግን፣ የሸማቾች ማህበር ለአምራቾች ከደላላ ዋጋ በላይ ቢያንስ 20 በመቶ ጨምሮ ለአርሶ-አደሩ መክፈልም ይገባዋል፡፡ የምንጊዜም ፍትሐዊው አሠራር ግን የአርሶ-አደሩን*

*መሸጫ ዋጋ በማምረቻ ዋጋ ላይ መመሥረት ነው፡፡ የለሙ አገሮች ዋጋ አወሳሰን ግን በማምረቻ ዋጋ፣ በሌለን በአቅርቦትና ፍላጎት ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ ዋጋ በልማዳዊ፣ በግድ-የለሽ አሠራር ወይም በደላላ መወሰኑ ሊቆም ይገባዋል፡፡*

(መ) *በአያሌ የክልል ከተሞች፣ (ለምሣሌ፣ **አዲስ አበባ፣ አርባ ምንጭ፣ ጎንደር፣ አዳማ፣ ድሬዳዋ፣ ሀረር፣ አሶሳ፣ ባህር ዳር፣ ፍኖተ ሰላም፣ ዱከም፣** ወዘተ...) ውስጥና በአካባቢያቸው የተለያዩ ፍራፍሬና አትክልት የማብቀል አመቺነትና ለገበያ የማቅረብ ሰፊ ዕድል አለ፡፡ ብዙ ሥራ-አጥ ወጣቶችና የቤት እመቤቶች በዚህ ሥራ ሊሠማሩና የገበያውን ዕጥረት አሚልተው ትልቅ የገቢ ምንጭ በማግኘት፣ ቀስ በቀስ ደግሞ ወደ አግሮ-ኢንስትሪም ሊሸጋገሩ ይችላሉ፡፡ **<u>መጀመሪያ ግን ከንቲባዎችንና ረዳቶቻቸውን ተስማሚ ቦታና መነሻ ድጋፍ በመስጠት ለዚህ የሥራ-አጥነት፣ የድህነትና የኑሮ ውድነት ቅነሳ ጥረት በማብቃት ብቁ መሪና ተባባሪ እንዲሆኑ ማስተማር ያስፈልጋል</u>**፡፡ ብዙ ገቢ ያለው የአዲስ አበባ አስተዳደር ምሣሌ ሊሆን ይችላል፡፡*

(ሠ) *በገጠሪቱ ኢትዮጵያ ባለፉት 28 ዓመታት የተፈጠረውን ሥራ-አጥነት ተከትሎ የመጣውን አደገኛ የቦዘኔ አዝማሚያ ለመቋቋም፣ ወደ ከተማ የሚደረገውን ፍልሰትና የውጭውን አስከፊና አደገኛ ስደት ለመግታት፣ በበሽታ የመለከፍንም አደጋ ለመቀነስ፣ የአገር ክብርም ለማስከበር፣ ለግብርና ሜካናይዜሽንና ለኢንዱስትሪ ዕድገት አዋጭ መሠረት ለመጣልና የገጠሩ ወገናችንን ሕይወት አፋጥኖ ለመለወጥ፣ በጃፓን፣ በቻይናና በሎችም የምሥራቅ እስያ አገሮች እንደተደረገው፣ በገጠሪቱ ኢትዮጵያ ምርት-ተኮር የልማት ተቋማትን በቀበሌ ልማት ድርጅት ውስጥ <u>ከሕዝቡ ጋር በመስማማት</u> ከፍቶ፣ መንደሮችን፣ ማዕከሉን፣ የጎረቤት ቀበሌ መንደሮችንና የወረዳውን መንገድ የሚያስተሳስር የመንደር መንገድ **<u>በተቀናጀ ሁኔታ ገንብቶና</u>** በፈረስ፣ ባህያ፣ በግመል ወይም በከብት የሚጎተቱ ጋሪዎች ፈብርኮ፣ የገጠርን ልማት ማፋጠን ይቻላል፡፡ የግብርና ምርት፣ የምርት ግባትና ሸቀጣ-ሸቀጥ በቀላሉ ማጓጓዝ እንዲቻል፣ ቢያንስ በበጋ ከዞን ከተማ መኪና ወደ ቀበሌ ልማት ድርጅት ያለችግር መግባት መቻል አለበት፡፡ **<u>ይህን ለማሳካት በድህነት ላይ በቁጭት የሚዘምት አገር-ወዳድና ብቁ የባለሙያ አመራር በሁሉም የአስተዳደር ደረጃ ማዘገጀት ያሻል</u>**፡፡ **<u>የክልል መሪዎችና የሚኒስትሮች ም/ቤት በብቃት መምራት አለባቸው</u>**፡፡ በውክልና መርህ ያልተገኙ የተቋማት መሪዎች የሙያና የአመራር ብቃት ወሳኝ ነወ።*

*ገና ሲጀምሩ፣ **የቀበሌ ልማት ድርጅቶች** እስከ 400,000 ወጣት፣ ውሎ አድሮ ደግሞ በሚሊዮን የሚቆጠር ወጣት ቀጣሪ ሊሆኑና ለአግሮ-ኢንዱስትሪ ልማቱም ሽግግር እርሾ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ በወፍጮ የገጠር ኢንዱስትሪ ልማቱ መጀመሩ በገጠር ሴቶች ላይ ከፍተኛ የቀን-ተቀንና የዘመናት አስከፊ የኑሮ ጫና ያቃልላል፡፡ የሴቶችን ወገኖቻችንን የተረፈ ጊዜና አቅምም፣ **<u>በጥንቃቄ በያካባቢው በተጠናና አዋጭ በሆነ የኤክስቴንሽን አገልግሎት</u>** ድጋፍ፣ ወደ ጓሮ አትክልት፣ ፍራፍሬ፣ ዶሮና እንስሳት-ተኮር ልማት በመምራት የገጠር ድህነትንና የከተማን የዋጋ መናር መቀነስ ይቻላል፡፡ የአርሶ-አደሩን ገቢና አገራዊ ምርትም ያሳድጋል፡፡ በቁጭት አገር ለማዘመን በቆረጠ አመራርና ሙያዊ ድጋፍ፣ ወፍጮውም በቀላሉ አትራፊ ይሆናል፤ የገጠርና የከተማ ሥራ-አጥነትም ይቀነሳል፡፡ ዘላለም በልማዳዊ አመራር መቀጠል ለአገር ሕልውና አደገኛ ነው፡፡*

(ረ) *ርካሽ ማጓጓዣ ጋሪዎችን፣ ከፉጉሎና የአካባቢ ግባቶች የተቀመሙ ማዳበሪያዎችንና የእህል ጎተራዎችን **<u>የቀበሌ ልማት ድርጅት የጥገና ማዕከል</u>** ፈብርኮ በድጎማ ለአርሶ-አደሮች ማቅረብ ይችላል፣ **<u>ብዙ ሥራ-አጥም ይቀጥራል</u>**፡፡ ድሀ አርሶ-አደሮች ማስቀመጫ ስለሚቸግራቸው፣ በተለይ ጋሪዎችና የግብርና መሣሪያዎች በማዕከሉ በጋራ ቢያዙና ፣ በዞኑ የቅርብ በጎና ሀቀኛ ቁጥጥር፣ በየምርት ዘመኑ በሎተሪ ሥርዓት (**ኢድልዎ እንዳይኖር**) በወጣ ተራ ከአጠቃቀም ጊዜያቸው እርዝመት ጋር የተጣጣመ የድጎማ ክፍያ (**ከመሥሪያ ዋጋው ጋር ተጣጥሞ በዞኑ ተወካይ መሪነት በአባላት ጉባዔ የሚወሰን ነው፡፡**) እየከፈሉ ቢጠቀሙ ይሻላል፡፡ ገቢያቸው ሲያድግ፣ በግል መግዛት ይችላሉ፡፡*

***የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲቱትም** ቀላል የግብርና መሣሪያዎችን (**መጥረያና መከስከሻ፣ መዝሪያ፣ ማጨጃ፣ መውቂያ፣ ጎተራ፣ የፀረ-ተባይና ውሀ መርጫ፣ የውሀ ፓምፕ፣ወዘተ**) ከመንግሥት የግብርና መሣሪያ ፋብሪካ ጋር በቅንጅትና በድጎማ አሠርቶና **<u>በሂደትም ይበልጥ እያሻሻለ</u>** ለአርሶ-አደሩ **የቀበሌ ልማት ድርጅት** በተራ እያዟዟሩ አባላት እንዲጠቀሙባቸው ሊያቀርብ ይችላል፡፡ ይህንን ማድረጉ ወሳኝ መሠረታዊ የልማት ድጋፍ ከመሆኑም በላይ ተጨማሪና ቋሚ የሥራ ዕድልም ይከፍታል፡፡ ለማንኛውም የግብርና መሣሪያ **<u>ዘላለም የውጭ ጥገኛ</u>** መሆኑ አያዛልቅም፡፡*

ከላይ የቀረቡት ምክረ-ሃሳቦች የተለመዱ አይደሉም፡፡ ነገር ግን፣ ዛሬ በገጠር ያለው ድህነትና የወጣት ሥራ-አጥነት በያመቱ እየተባባሱ ከሄዱ፣ ምንም ኃይል ሊቋቋመው የማይችል አገር-አቀፍ ነውጥ አይቀሬ ነው፡፡ ችግራችን በኋላ-ቀርነታችን ተቆጭተን ግብርና-መር ዕድገት ለማሳካት አለማለማችን ሳይሆን፣ ለኢኮኖሚው መሠረት ለሆነው ለገጠር አገራችን ቅድሚያ ባለመስጠትና በአብዛኛው በመኪና ምርጫ፣ በጉንጭ-አልፋ ስብሰባ፣ በቢሮና ከተማ ማብለጭለጭ ውድድር ተገድበን ለ85 በመቶ የአገራችን ሕዝብ ዕድገት ያለን ቁርጠኛነት በማነሱ፣ የዕድገታችን ቅደም-ተከተል ያልተስተካከለ ሆነና ***<u>ኋላ-ቀር ግብርናችንን ዘላለም የዕድገት መነሻና መድረሻ በማድረግ ድህነታችን በየዓመቱ እየከፋም ሲሄድ እየተላምድነው ዘመናትን መግፋታችን ነው</u>***፡፡

የሰው ኃይል፣ ለም መሬትና ሰፊ የውሀ ሀብትም አለን፡፡ የእህል ሰብል፣ እንሰት፣ ጥራጥሬ፣ የቅባት እህሎች፣ ቅመማ-ቅመም፣ አትክልት፣ ሻይ፣ ፍራፍሬ፣ ቡና፣ ጥጥ፣ ሌላም ማምረት እንችላለን፡፡ ዛሬም ከሞፈር-ቀንበርና ኋላ-ቀር ማረሻ ጋር ተጣብቀን፣ የከብት ግጦሽ ፍለጋ ከቦታ ቦታ ባዝነን፣ በእናቶች ጀርባ በሚታዘል ቅምባና በአህያ ማጓጓዣ ተወስነን፣ በልቶ ማደር የቸገረው ሕዝብ በሚከፍለው ታክስ፣ በንጉሡ ዘመንም ባልታየ ሁኔታ፣ ለሹማምንቱ የተጌጠና በሶፋ የተሞላ አውላላ ቢሮ ከምርጥ መኪና፣ የቀለም ቴሌቪዥንና ከልዩ ልዩ ጥቅማ-ጥቅሞች ጋር ሰጥተን፣ በተለይም ባለፉት 45 ዓመታት፣ የገጠር ዕድገት ለማምጣት **<u>ቁርጠኛነትና ወገናዊ ቁጭት አጥሮን</u>** ፣ ዛሬም ኋላ-ቀርና ድሀ አገር ነን፡፡

ኋላ-ቀርነት የሰፈነብን፣ 35 በመቶ የአገር ምርት ባለቤት የሆነውን፣ 80 በመቶ የውጭ ምንዛሪ አምራቹን፣ 80 በመቶ የአገሪቱን ሠራተኛ የያዘውን፣ ለአገር ነፃነትም ጋሻ የሆነውን **<u>85 በመቶውን የኢትዮጵያ ሕዝብ</u>** የኢኮኖሚ ዕድገት ባግባቡ ባለመምራታችንና ድህነትን ያልቀረፉ ስልቶች ባለፉት 45 ዓመታት በተከታታይ በመተግበራችን ነው፡፡ ምስክሩም የዛሬው ኋላ-ቀርነታችን ነው፡፡

የኢኮኖሚያችን መሠረት የሆነው የገጠር ወገናችን እንደ ሩቅ ምሥራቅ አገሮች ፈጣን የኢንዱስትሪ ሽግግር ለማምጣት የሚያስችል አቅም አለው፡፡ **<u>አፍሪቃና አብዛኛው እስያ በቅኝ አገዛዝ ሥር ሲወድቅ፣ በብቁ ዝግጅት፣ ቆራጥና ሥልታዊ አመራር ዘመናዊ የአውሮጳ እብሪተኛ ወራሪ ጦር ያንበረከኩት ጀግና አርሶ-አደርና አርብቶ-አደር አባቶቻችን ልጆችና የልጅ-</u>**

**ልጆች** ዛሬም እንደ አድዋው ፈታኝ ትግል የተሟላ ዝግጅት፣ ቆራጥና በሳል ሥልታዊ አመራር ካገኙ፣ በድህነት ላይ ፈጣንና አንፀባራቂ ድል ለመቀዳጀት አቅሙ አለ፡፡ **በኋላ-ቀርነታችን ከልብ የተቆጨ አገር-ወዳድና ብቁ የባለሙያ አመራር በየዘርፉ** ካገኙ፣ እንደ ሜጂ ጃፓን በ 14 ዓመት [5] ዘመናዊ የኢኮኖሚ መሠረት ባይገነቡም፣ የኢትዮጵያን ገጠር፣ **እንዲያም ሲል ሙሉ ኢትዮጵያን**፣ ከድህነት ለማውጣትና ጽኑ የገጠር አግሮ-ኢንዱስትሪ መሠረት በመገንባት **የወጣቱንም እስጊ ሥራ-አጥነትና ሰደት፣ የእርሻ መሬት መጣበብም** ችግር ለማስተካከል ብዙ ጊዜ አይወስዱም፡፡

**ሕዝባችን በቁጭትና በትጋት፣ በብቁና አገር-ወዳድ ባለሙያ ከተመራና ከበቂ የገጠር ልማት ባጀትና ዕውቀት ጋር ሌት ተቀን ከተሠራ**፣ ከታታሪ የገጠር ልጆቿ፣ ከለምለም መሬቷና ሰፊ የውሀ ሀብቷ ጋር፣ ኢትዮጵያችን ለማንም ባለዕዳ ሳትሆን፣ ከማንም ስነዴ ግዢ ከአህጉር ወደ አህጉር ሳትንከራተት፣ አንድም ዜጋ ሳይዋረድና ሳይሰደድ፣ ለአደገኛም ወረርሽንኝ ሳይጋለጥና ሳያጋልጠን፣ ትምህርትንና የገጠር ልማትን ከልብ ካስቀደምን፣ ፈጣን የገጠር ልማት ዕድገት በአጭር ጊዜ ማሳካት ትችላለች፡፡ ለዚህ አባባል፣ አአአ የ 1860 ዎቹ ጃፓንና የ 1860 ዎች የአሜሪካ ባለ ***LAND GRANT COLLEGES*** ምስክር ናቸው።

ከላይ የቀረበው ይደገምና፣ **ሜጂ ጃፓን ለአያሌ ዘመናት የተገዛችበትን ዘመነ መሣፍንት ከቂም-በቀል በፀዳና አገር ገንቢ በሆነ መንገድ ለውጣ፣ ለወረሰችውም ንብረት ሁሉ ካሣ ከፍላ የአገር ግንባታ ስትጀምር፣ አንድም ዩኒቬርሲቲ፤ አንድም ባንክ፣ አንድም ዘመናዊ ፋብሪካ፣ አንድም ዘመናዊ አስተዳደርና ንግድ ሳይኖራት፤ ይኸ ነው የሚባል FDI ሳታስተናግድ፣ አንድም ዘመናዊ መንገድ፣ ስልክ፣ የፖስታ አገልግሎት፣ባቡር፣ መኪና፣ አውሮፕላን የሚባል ሳይኖራት፤ ቅንጣት መሬት ለማንም የውጭ ኢንቬስተር ሳትሰጥ፣ በዋናነት <u>በሩዝ፣ ሀርና ሻይ ምርቶች ላይ ብቻ ተመርኩዛ</u>፣ <u>ሌት ተቀን በሠሩ</u> <u>አገር-ወዳድና ጀግና መሪዎቿና ልጆቿ</u> ያላሰለሰ ጥረት ብቻ እአአ በ1868 ግንባታ ጀምራ በ14 ዓመት ውስጥ የጃፓንን ዘመናዊ የኢኮኖሚ መሠረት ገንብታለች** [5] ፡፡

ኢትዮጵያችን ከደጋ እስከ ቆላ በስፋት ሊመረቱና ለማንኛውም ገበያ ፈጥነው ሊቀርቡ የሚችሉ ብዙ ሰብሎች (***ጤፍ፣ ስንዴ፣ ቦቆሎ፣ በሎቄ፣ ሰሊጥ፣ ገብስ፣ አኩሪ አተርና አያሌ ጥራ-ጥሬዎች፣ ወዘተ***)፣ ብዙ ዓይነት ፍራፍሬ (***ኮክ፣ ማንጎ፣ አፕል፣ ሙዝ፣ ሎሚ፣ ወይን፣ ፕሩን፣ አቮካዶ፣ ጊሽጣ፣ ፓፓያ፣ ማንደሪን፣ ትርንጎ፣ ወዘተ***)፣ ብዙ ዓይነት የቅባት እህሎች (**ኑግ፣ ተልባ፣ ጎመን ዘር፣ ሱፍ፣ ለውዝ፣ ጫቅማ**)፣ ምርጥ ቡና፣ ሻይ፣ ቅመማ-ቅመም፣ ጥጥና ሌሎችም ለአግሮ-ኢንዱስትሪ ግባት የሚሆኑ የማምረት ዕድልና ዘመናዊ የልማት ጅማሮም እያላት፣ **ከ45 ዓመት የወጣት "ተራማጅ " አገዛዝም በኋላ**፣ ዛሬም ኋላ-ቀርና በማንኛውም የልማት መስክ የውጭ ጥገኛ መሆኗ **<u>ተማርን የሚሉትን አገር-ወዳድ "ባላገሮች " ሁሉ ሊያስቆጭና ሊያንገበግብ ይገባል</u>**፡፡

ብዙ አገሮች ከ30 ዓመት ባነሰ ጊዜ ያሳኩትን ልማት፣ እኛ በ45 ዓመትም አለማሳካታችን ለዚህ ትውልድና ለጥቁር ዘር መኩሪያ ለነበረችውም ኢትዮጵያችን ሀፍረት ነው፡፡ ባግባቡ በልቶ የማያድር ምዝብር ሕዝብ ለመግዛት መሻኮቱና አገርን ሰላም መንሳቱ ድህነትን ስለሚያባብስና በኢትዮጵያና በኢትዮጵያዊነት ላይ የጥፋት ዘመቻ ላቀዱትም ትልቅ ድጋፍ በመሆኑ፣ **<u>በሃይማኖት አባቶችና በሽማግሎች ምክር ሳይሆን በቆራጥ፣ ጠንካራና አስተማማኝ ሕጋዊ መንግሥታዊ ኃይል የጥፋት ኃይሎች የሆኑ ሁሉ ለሕግ ተገዢ ሊደረጉ ይገባል</u>**፡፡ **<u>መንግሥት ብቸኛው የታጠቀ ኃይል የሆነው ይህንንም ለማስፈጸም ነው</u>**፡፡

ሰላማችንን አረጋግጠን፣ ከላይ እስከ ታች ዓለቃና ምንዝር ሳይባል፣ የግል ጥቅምና ምኞት ሳያደናቅፉን፣ ቅን ባላሰቡ ሰዎች በተደገሰልን የጎሣና የሃይማኖት ክፍፍል ሳንጠለፍ፣ ሌት ተቀን ተባብረን ከገጠሩ ሕዝብ ጋር ከሠራንና **<u>ግብርናውን፣ የትምህርት ስምሪቱንና የትምህርት ጥራቱን አፋጥነን ዓላማ-ተኮረ አድርገን ካሳደግን</u>**፣ ኋላ-ቀርነትንና ድህነትን ለማሸነፍ ስለምንመቻች፣ ሀብታምና የማትደፈር ኃያል ኢትዮጵያን ማውረስ እንችላለን፡፡ ምን ጊዜም፣ ያለገጠር ልማትና ዓላማ-ተኮር ትምህርት ዕድገት አይታሰብም፡፡ በ45 ዓመት ጉዞ ውስጥ ከ45 በላይ ዩኒቬርሲቲዎች ተገነቡ ቢባልም፣ ዛሬም ሕዳሴ ግድብንና አዲሱን ባቡር ያስገባነው ከውጭ በተገዙ ኩባንያዎች ነው። ይህም፣ ከግብርናው ማሳደግ ጋር፣ የትምህርት ሥርዓት ለውጥ እንደሚያስፈልግ በቂ ምስክር ነው።

### ዋቢ መጻሕፍት


1. የግብርና ሚኒስቴር (2011) *የግብርና ዘርፍ የ 2012 ሥራ ዕቅድ* ፡፡ ግብርና ሚኒስቴር፣ አዲስ አበባ፡፡
2. የግብርና ሚኒስቴር (2011)፡፡ *የግብርና ዘርፍ 2011 በጀት ዓመት የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት*፡፡ ግብርና ሚኒስቴር፣ አዲስ አበባ፡፡
3. የግብርናና እንስሳት ሀብት ሚኒስቴር (2011)፡፡ *የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ 2 የ2010 በጀት ዓመት የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት* ፡፡ የግብርናና እንስሳት ሀብት ሚኒስቴር፣ አዲስ አበባ፡፡
4. Abate Meseret Chanie, Kuang Yuan Pei, Zhang Lei, Cai Bao Zhong (2018). Rural Development Policy: What does Ethiopia need to ascertain from China rural development policy to eradicate rural poverty? *American Journal of Rural Development,* Vol. 6, pp. 79-93. Science and Educational Publishing.
5. Allen, G.C. [1962]. *A Short Economic History of Modern Japan: 1867-1937.* George Allen & Unwin Ltd. London.
6. Andinet Woldemichel, Adeleke Salami, Adamon Mukasa, Anthony Simpasa and Abebe Shimeles (2017). Transforming Africa's Agriculture through Agro-industrialization. *Africa Economic Brief,* Vol. 8, Issue 7.

7. Bredo, William (1959). Rural Industrialization for Agricultural development. *Journal of Farm Economics*, pp. 1332-1344.
8. CERI Staff Report (2011). Crop Subsidies in Foreign Countries: Different Paths to Common Goals. *Cotton Economics Resarch Institute,* Department of Agriculture and Applied Economics, Texas Tech University, Lubbock, USA.
9. Christopher Chibwana and Monica Fisher (2010). The Impacts of Agricultural Input Subsidies in Malawi. International Food Policy Research Institute. *Policy Note #5*. Washington, D.C.
10. Department of Agriculture, Forestry and Fisheries (2012). *Briefing on Tariffs and Subsidies in Agriculture, Forestry and Fisheries*. South Africa.
11. Dessalegn Rahmato (ed) (2018) *Land, Landlessness and Poverty in Ethiopia: Research Findings from Four National regional States.* Forum for Social Studies. Addis Ababa, Ethiopia.
12. Diriba Welteji (2018). A Critical Review of Rural Development Policy of Ethiopia: Access, Utilization and Coverage. *Agriculture and Food Security*, 7:55.
13. IFAD (2016). *Rural Development Report 2016.* Rome, Italy.
14. Kenichi Ohno (2009). *ADLI and Future Directions for Induatrial Development.* Conference Presentation.
15. Mervyn Piesse (2017). *Agricultural Subsidies in China: Increasing Mechanization, Cutting Waste and Cleaning the Environment.* Global Food and Water Crises Research Programme.
16. Ministry of Agriculture and Natural Resources (2017). *Agricultural Extension Strategy of Ethiopia.* Addis Ababa.
17. Pak K. Lee and C.C.L Kwong (2000). China's Rural Industrialization at the Turn of the Century: Taking Stock, Looking Ahead. *China Review*, pp. 359 – 379.
18. Wikipedia (2017). *Common Agricultural Policy of the European Union.*
19. Wikipedia (2018). *United States Farm Bill.*
20. World Bank (2005). *Agriculture, Rural Development and Pro-poor Growth: Country experiences in the Post-Reform Era.* Agriculture and Rural Development Discussion Paper 21. Washington, D.C.
21. Yingyi Qian (2017). *How Reform Worked in China: The Transition from Plan to Market.* The MIT Press, Cambridge, Massachusetts, USA.